

fetena.net : Ethiopian online exas and textbooks

# አካባቢ ሳይንስ

## አንደኛ ክፍል

## የተማሪ መጽሐፍ













አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# አካባቢ ሳይንስ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 1ኛ ክፍል


አዘጋጅ፡- አበባ ገብረመስቀል
ዮዲት መከተ

አርታኢ፡- ብርሃኑ ሀብተማሪያም
መድሃኔ እቁባሚካኤል

ገምጋሚዎች፡- ደስታ መርሻ ኦዳ
ብርሃኑ ፍቅሩ ፍሬሰንበት
መኮንን ስገሠ ታችበሌ
ሰሎሞን ወንድሙ መታፈሪያ
ግርማ መንግሥቱ ጥሩነህ



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
2006 ዓ.ም

© 2006 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

ይህንን መጽሐፍ ከተዘጋጀበት ዓላማ ውጭ በከፊልም ይሁን በሙሉ በኅትመት ወይንም በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ወይንም በየትኛውም መንገድ ያለ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ማባዛትና አስመስሎ ማራባት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር ፬፻፲/፲፱፻፺፮ ዓ.ም. በአደቀው የቅጅና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ ሕግ አዋጅ መሠረት ያስቀጣል::

**የመጽሐፉ አዘጋጅ፡- ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**

☎ +251 111 224 504
+251 111 224 505

E-mail: kurazpublisher@gmail.com
kurazpublisher@yahoo.com

✉ 100767
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

# ማውጫ

ገፅ


## ምዕራፍ 1. እኛነታችን

1.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍላችን .....2
1.2 መሠረታዊ ፍላጐቶች .....7
1.3 ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የታወቁ በሽታዎች .....13
1.4 አምስቱ የስሜት አካላት .....22
ማጠቃለያ .....35
የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች .....37
ፍተሻ .....38

## ምዕራፍ 2. ቤተሰባችን

2.1 የቤተሰብ አባላት .....40
2.2 ስቤተሰባችን፣ ምግብ፣ መጠለያና፣ ልብስ ያስፈልጋል .....46
2.3 የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች .....53
ማጠቃለያ .....62
የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች .....63
ፍተሻ .....64

## ምዕራፍ 3. ትምህርት ቤታችን

3.1 የትምህርት ቤታችን ግቢ .....66
3.2 ህጐችና ደንቦችን እናክብር .....71
3.3 ጥሩ የእርስ በእርስ ግንኙነት አስን.....73
3.4 የመንገድ ደህንነት .....75
3.5 በት/ቤታችን ስማከናወን የምንችላቸው እንቅስቃሴዎች
ወረቀት በመጠቀም መሳይ ቅርፃችን መሥራት .....79
ማጠቃለያ .....81
የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች .....82
ፍተሻ .....83

## ምዕራፍ 4. ወረዳችን


4.1 የወረዳችን መገኛ ..... 85

4.2 በዙሪያችን የሚገኙ ህይወት የሌላቸው ነገሮች ..... 89

4.3 በዙሪያችን የሚገኙ ህይወት ያላቸው ነገሮች ..... 95

4.4 በአካባቢያችን የተለመዱ የሥራ እንቅስቃሴዎች ..... 104

4.5 የአካባቢያችን መጓጓዣ ..... 108

ማጠቃለያ ..... 112

የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች ..... 113

ፍተሻ ..... 114

# ምዕራፍ አንድ

## እኛነታችን

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ስሞች ትጠራላችሁ፣ የእያንዳንዳቸውን ተግባራት ትናገራላችሁ፣ ጥንቃቄም ታደርጋላችሁ፡፡
- ሶስቱን መሰረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎቶች በመዘርዘር ጥቅሞቻቸውን ታስረዳላችሁ፡፡
- አንዳንድ በአካባቢው የሚታወቁ በሽታዎችን በመዘርዘር መከላከያ ዘዴዎቻቸውን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- የአምስቱን የስሜት አካላት ስሞች በመጥቀስ የእያንዳንዳቸውን ተግባራት ስረዳላችሁ፣ በተግባርም ታሳያላችሁ፡፡
- አንዳንድ የብርሃን፣ የድምፅ፣ የቀለም፣ የጣዕምና የሽታ ምንጮችን ቀለል ያሉ ሙከራዎች በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎቶችን ማለትም፡- መመልከትን፣ መጠየቅን፣ መግባባትንና በቡድን መስራትን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡

## 1.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍላችን

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች**


**ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦**

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችሁን ስሞች ትጠራላችሁ።
- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችሁን እየጠቆማችሁ (እየነካችሁ) ታሳያላችሁ።
- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችሁን ተግባራት ትናገራላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች
- የሰውነት ክፍሎች ተግባራት

### 1.1.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች




ሥዕል 1.1 ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች

**ስዕል 1.1ን በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::**

1. ተማሪዎች! ስዕሉ የምን ስዕል ይመስላችኋል?
2. ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
3. ልጁ ስንት እጆች አሉት?
4. ልጁ ለመራመድ የሚጠቀምበት የአካል ክፍል የትኛው ነው?

**ተማሪዎች! ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ምን ምን እንደሆኑ ተረዳችሁ?**

**ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚባሉት:- ራስ፣ ፀጉር፣ ጆሮ፣ አይን፣ አፍንጫ፣ እጅ፣ ጣት፣ ደረት፣ ሆድ፣ ወገብ፣ ቅልጥም፣ ጉልበት፣ እግርና የመሳሰሉት ናቸው::**

## መልመጃ 1.1

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::**

1. ከአንገት በላይ ያሉትን ውጫዊ የአካል ክፍሎች ዘርዝሩ::
2. ከአንገት በታች ካሉት ውጫዊ የአካል ክፍሎች ውስጥ የምታውቋቸውን ስም ጥሩ::

### 1.1.2 የውጫዊ ሰውነት ክፍሎች ተግባራት

**ተማሪዎች! ስለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ተግባራት መዘርዘር ትችላላችሁ?**

**የውጫዊ ሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መለየት**

**በጫወታ መልክ ውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት ማጥናት**

1. **አሥር አሥር ተማሪዎች በመሆን ቡድን መሥርታችሁ በየቡድናችሁ የውጫዊ የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት በመዘርዘር ፃፉ::**
2. **መምህራችሁ ለየቡድኑ ዕድል ሲሰጡ ቡድኑን የሚወክለው አንድ ተማሪ ስለ አንድ ውጫዊ የሰውነት ክፍል ተግባር ሲገልጽ ሌሎቹ የክፍል ተማሪዎች ደግሞ ስለየትኛው የሰውነት ክፍል እንደተገለጸ ይናገራሉ:: በዚሁ መሠረት ለቡድኖች በየተራ ዕድል እየተሰጠ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት በጫወታ መልክ አጥኑ::**




ልጁ ምን እያደረገ ነው?



ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?



ወገብ አጎንብሶ ስራን ለመስራት ይጠቅማል



እግር ለመራመድ ወይም ለመሮጥ ያገለግላል

ሥዕል 1.2 የሰውነት ክፍሎች ተግባራት


## መልመጃ 1.2

በ"ሀ" ስር የቀረቡትን የአካል ክፍሎች በ"ለ" ስር ከቀረቡት ተግባራት ጋር በመስመር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እጅ | ለማየት |
| 2. ፀጉር | ለመራመድ |
| 3. አይን | ለማሽተት |
| 4. እግር | ራስን ለመሸፈን |
| 5. አፍንጫ | ዕቃን ለማንሳት |

### 1.1.3 ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚደረግ ጥንቃቄ

ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል። ለምሳሌ ከዚህ በታች ያሉትን ስዕሎች ተመልከቱ።



የህፃኑ እናት ምን እያደረገች ነው?



ስዕሉ ምንን ያሳያል?



ልጅቷ ምን እያደረገች ነው?



ከስዕሉ ምን ትረዳላችሁ?



ልጁ ምን እያደረገ ነው?



በሥዕሉ የሚታየው ልጅ ምን እያደረገ ነው?



ስዕሉ ምንን ያሳያል?



ልጅቷ ምን እያደረገች ነው?

ሥዕል 1.3 ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚደረግ ጥንቃቄ

ተማሪዎች ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን ምን ምን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን ተገነዘባችሁ?

ለውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችን ጤንነት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይኖርብናል፡፡

1. እጅን፣ እግርን፣ ፊትንና፣ ፀጉርን መታጠብ
2. ገላን መታጠብ
3. የአፍንጫንና የጆሮን ፅዳት መጠበቅ
4. ጥፍርን መቁረጥ
5. ፀጉርን ማበጠር

**ተማሪዎች!** ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችንን ማፅዳት ይገባናል፡፡ እስኪ ልጆች ንፅህናን ከመጠበቅ አንፃር የውኃን ጥቅም ተናገሩ፡፡

## መልመጃ 1.3

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. ከሚከተሉት ውስጥ ከአንገት በላይ ያለው የአካል ክፍላችን የቱ ነው?
   ሀ. ሆድ ለ. እግር ሐ. ደረት መ. አይን
2. ራሳችንን ከብርድ ለመከላከል የሚረዳን የቱ ነው?
   ሀ. ቅንድብ ለ. ጆሮ ሐ. ፀጉር መ. ግንባር

**ለ. በ «ሀ» ስር የተዘረዘሩትን የሰካል ክፍሎች በ«ለ» ስር ከተዘረዘረው ጥቅማቸው ጋር በመስመር አዛምዱ::**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አንገት | ለመቅመስ |
| 2. ምላስ | ዞሮ ለማየት |
| 3. ጥርስ | ለማኘክ |
| 4. ጆሮ | ለመስማት |

**ሐ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ፡፡**

1. ከምግብ በፊትና ከምግብ በኋላ እጅን መታጠብ አስፈላጊ ነው፡፡
2. የእጅና የእግር ጥፍሮች ቢያድጉም በጤናችን ላይ ጉዳት አያመጡም፡፡
3. እግርን በየቀኑ መታጠብ ያስፈልጋል፡፡

**መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. ፀጉርን መታጠብ ለምን ይጠቅማል?
2. አፍንጫ በምን ይፀዳል?
3. ምግብ ከመመገባችን በፊት ምን ማድረግ አለብን?

## 1.2 መሠረታዊ ፍላጐቶች

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡- |
| • ሶስቱን መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጐቶች ትዘረዝራላችሁ፡፡ |
| • ስለሶስቱ መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጐቶች ጥቅም ታስረዳላችሁ፡፡ |

**ቁልፍ ቃላት**

- መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎቶች
- መጠለያ
- ምግብ
- ልብስ

### 1.2.1 ሶስቱ መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጐቶች

ተማሪዎች! ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች በደንብ ተመልከቱ፡፡





ምግብ ስአድገት ይጠቅማል




ልብስ አካልን ይሸፍናል



ቤት ከዝናብ፣ ከፀሃይና ከአደጋ ይከላከላል

ሥዕል 1.4 የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች

የሰው ልጅ ለመኖር ሶስት መሠረታዊ ነገሮች ሊሟሉለት ይገባል።

ሶስቱ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች ምን ምን እንደሆኑ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

**ተማሪዎች! የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች ምን ምን እንደሆኑ ከሥዕሎቹ ተረዳችሁ?**

ሶስቱ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች የምንላቸው፡-

1. ምግብ
2. ልብስና
3. መጠለያ ናቸው።

**ከነዚህ መሠረታዊ ፍላጐቶች አንዱ እንኳን ቢጐድል ምን የሚያስከትል ይመስላችኋል? ሐሳባችሁን ለመምህራችሁ ግለጹ።**

## 1.2.2 መሠረታዊ ፍላጐቶችና ጠቀሜታቸው

### ሀ. ምግብ

- **ተማሪዎች ስለ ምግብ ምንነት ታውቃላችሁ?**
- **በጣም የምትወዱት የምግብ ዓይነት ምንድነው?**

**ተማሪዎች! ከዚህ በታች የቀረቡትን ስዕሎች በደንብ ተመልከቱ።**





**ሥዕል 1.5 የምግብ ጥቅም ለአካላዊ እንቅስቃሴ**

**ከስዕሎቹ ምን ተረዳችሁ?**

**ምግብ:-** - ለጤንነት

- ለአካላዊ ዕድገት
- ሙቀትና ጉልበት ለማግኘት ይጠቅማል።

**ተማሪዎች!** የምግብ መለያ ባህርያት ምን ምን እንደሆኑ ለመምህራችሁ ንገሩ።

የምግብ መለያ ባህርያት አራት ናቸው።

እነርሱም፡-

1. ጣዕም ---------- ጣፋጭ፣ ኮምጣጣ
2. ሁነት ---------- ፈሳሽ፣ ጠጣር
3. ቀለም ---------- ነጭ፣ ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ
4. መአዛ ---------- ጥሩ ሽታ፣ መጥፎ ሽታ ናቸው።

## ለ. ልብስ

ተማሪዎች ልብስ ለምን ለምን ይጠቅማል?

**የሚከተሉትን ሥዕሎች በደንብ ተመልከቱ።**



- በስዕሉ የሚታየው ልብስ ምንድነው?



- ይህ ምን ዓይነት ልብስ ነው?



- ይህ ልብስ ምን ይባላል?
- ከምን የተሠራ ይመስላችኋል?



- በስዕሉ የሚታየው ልብስ ምንድነው?



- በስዕሉ የምታዩት ልብስ ምንድን ነው?



- ይህ ልብስ ምንድን ነው?
- ምን ጊዜ የሚለበስ ይመስላችኋል?



- የዚህ ልብስ መጠሪያ ስም ምንድን ነው?
- ለምን አገልግሎት የሚውል ይመስላችኋል?

**ሥዕል 1.6 የተለያዩ የልብስ ዓይነቶች**

**ተማሪዎች! ልብስ ከምን ከምን የሚሰራ ይመስላችኋል?**

**ልብስ** 1. በተፈጥሮ ከሚገኙ ጥሬ ዕቃዎች

**ለምሳሌ፦** ሀ. ከጥጥ

ለ. ከቆዳ

ሐ. ከበግ ፀጉር (ከሱፍ) ይሰራል።

2. ከሰው ሠራሽ ጥሬ ዕቃዎች

**ለምሳሌ፦** በፋብሪካ ከተመረተ ጨርቅ መሥራት ይቻላል።

## መልመጃ 1.4

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1. ከቆዳ ምን ምን ዓይነት ልብሶችን መስራት ይቻላል?
2. ከጥጥ ምን ምን ዓይነት ልብሶች እንደሚሰሩ ተናገሩ።
3. ከበግ ፀጉር ምን ምን ዓይነት ልብሶች ይሠራሉ?
4. በስዕል 1.6 ላይ የሚገኙትን ስዕሎች በመመልከት ከምን ከምን እንደሚሰሩ ተናገሩ።

**የልብስ ጥቅም**

**ተማሪዎች! ልብስ ምን ምን ጥቅም እንደሚሰጥ ለመምህራችሁ ንገሩ።**

**ከዚህ ቀጥሎ የሚገኙትን ስዕሎች በመመልከት የትኛቹ የልብስ ዓይነቶች በየትኛቹ ጊዜያት እንደሚለበሱ ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ።**



ስዕል 1.7 የልብስ ጥቅም

**ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት የልብስ ጥቅሞች ናቸው፡፡**

- ከብርድ፣ ከፀሐይና ከዝናብ ለመከላከል
- ለውበት ወይም ለጌጥ
- ገላን ለመሸፈን

## መልመጃ 1.5

**ከዚህ በታች በ«ሀ» ሥር የተቀመጡትን የልብስ ጥቅሞች በ«ለ» ሥር ከተቀመጡት የልብስ ዓይነቶች ጋር በመስመር አዛምዱ፡፡**

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. ብርድን ለመከላከል የሚለበስ ልብስ | ሀ. ነጭ ሸሚዝ |
| 2. ዝናብን ለመከላከል የሚለበስ ልብስ | ለ. ወፍራም ጋቢ |
| 3. ሙቀትን ለመቀነስ የሚለበስ ልብስ | ሐ. የዝናብ ልብስ |

### ሐ. መጠለያ

**ተማሪዎች!** *መጠለያ ማለት ምን ማለት ነው?*

በአካባቢያችሁ የሚገኙትን የመጠለያ ዓይነቶች ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

መጠለያ ማለት ሰዎች ተሰባስበው የሚኖሩበት (የሚጠለሉበት) ቤት ማለት ነው፡፡

### የመጠለያ ጥቅሞች

**ተማሪዎች ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች ተመልከታችሁ የመጠለያን ጥቅም ለመምህራችሁ ግለፁ፡፡**



- በሥዕሉ የምትመለከቱት ቤት ምን ጥቅም እየሰጠ ነው?



- በሥዕሉ የምትመለከቱት የዱር እንስሳ በቤቱ ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች በቀላሉ ለማጥቃት የሚችል ይመስላችኋል?

**ሥዕል 1.8 የመጠለያ ጥቅም**

**ተማሪዎች!** በአጠቃላይ መጠለያ፡-

1. ከዝናብ
2. ከፀሐይ
3. ከአውሬ (አደጋ ከሚያደርስ የዱር እንስሳ)
4. ከንፋስና ከመሳሰሉት ለመከላከል ይጠቅማል።

**መጠለያዎች፡-**

- ከሣር
- ከሲሚንቶ
- ከቆርቆሮ
- ከአሸዋ
- ከሸክላ
- ከብረት
- ከጭቃ
- ከብሎኬት
- ከእንጨት ሊሠሩ ይችላሉ



ሀ. ከቀርከሀ የተገነባ የሣር ክዳን ቤት



ለ. በእንጨትና በጭቃ የተገነባ የቆርቆሮ ክዳን ቤት



ሐ. በሸክላ የተገነባ የቆርቆሮ ቤት



መ. በብሎኬት የተገነባ ፎቅ

**ሥዕል 1.9 የቤት ዓይነቶች**

## መልመጃ 1.6

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ።**

1. ጋቢና ነጠላ ከጥጥ ይሠራሉ።
2. ቤትን ከእንጨት፣ ከሣርና ከጭቃ መስራት ይቻላል።
3. መጠለያ ከፀሐይና ከዝናብ ይከላከላል።
4. ምግብ በህይወት ለመኖር አስፈላጊ ነው።
5. ምግብ ልብስና መጠለያ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶች ናቸው።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።**

1. ከሚከተሉት ውስጥ በብርድ ጊዜ የሚለበሰው የትኛው ነው?
   ሀ. ሸሚዝ ለ. ጋቢ ሐ. ካናቴራ መ. የናይለን ልብስ
2. ልብስ የሚሠራው
   ሀ. ከጥጥ ለ. ከቆዳ ሐ. ከናይለን መ. ከሁሉም
3. ከሚከተሉት ውስጥ ኮምጣጣ ጣዕም ያለው የቱ ነው?
   ሀ. ሙዝ ለ. ሎሚ ሐ. ፓፓያ መ. ሽንኮራ አገዳ
4. ከሚከተሉት ውስጥ የመጠለያ ጥቅም ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ከአደገኛ ዱር እንስሳት መከላከል ሐ. ከዝናብ መከላከል
   ለ. ገላን መሸፈን መ. መልሱ የለም

**ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጐቶችን ዘርዝሩ።
2. የመጠለያ ጥቅሞችን ዘርዝሩ።
3. የምትማሩበት ክፍል ከምን የተሠራ ነው?
4. ምግብ ለምን ለምን ይጠቅማል?

## 1.3 ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የታወቁ በሽታዎች

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦<br>• ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የታወቁ በሽታዎችን ስም ትጠቅሳላችሁ።<br>• የታወቁ በሽታዎችን ለመከላከል የሚረዱ ቅድመ ጥንቃቄዎችን ትገልፃላችሁ። |


## ቁልፍ ቃላት

- ህመም
- ተላላፊ በሽታ
- ተላለፊ ያልሆነ በሽታ

ተማሪዎች! የሚከተሉትን ስዕሎች በደንብ ተመልከቱ። ከስዕሎቹ ምን ተረዳችሁ?



ጤነኛ ልጅ



ታማሚ ልጅ

ሥዕል 1.10 ጤነኛና ታማሚ ልጆች

የተለያዩ በሽታዎች በሰዎች ላይ ጉዳት ያደርሳሉ።

ተማሪዎች! ህመም ምንድን ነው? ጤና ማለትስ ምን ማለት ነው? ከዚህ በፊት ታማችሁ ታውቃላችሁ? በታመማችሁ ጊዜ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማችሁ ነበር? መልሱን ለመምህራችሁ ንገሩ።

መታመም ማለት የጤንነት መጓደል ማለት ነው። ህመም ሲኖር ደግሞ በአካልና በአእምሮ ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል።

የጤና መጓደል ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

ሰውነታችንና አእምሮአችን በትክክል ከሠራ ሙሉ ጤነኞች ነን እንላለን። ሁላችንም ደስተኛ ኑሮ ለመኖር እንፈልጋለን። ደስተኛ ኑሮ ለመኖር ደግሞ ጤናችን የተሟላ መሆን አለበት።

ተማሪዎች! ጤንነታችን የተሟላ ከሆነ

- ጨዋታ ለመጫወት
- የፈለግነውን ሥራ ለመሥራት
- በአግባቡ ትምህርታችንን ለመማር እንችላለን።

- ጤነኞች ካልሆንን ምን ዓይነት ችግሮችን የሚያስከትልብን ይመስላችኋል?
- በሽታ ማለት ምን ማለት ነው?

በሽታ የውስጥ ወይም የውጭ አካላችንን በመጉዳት ሰውነታችን የዕለት ተዕለት ተግባሩን በትክክል እንዳያከናውን የሚያደርግ የጤና መታወክ ነው።

በሽታ በሁለት ይከፈላል። እነርሱም

ሀ. ተላላፊ በሽታና

ለ. ተላላፊ ያልሆነ በሽታ ናቸው።

## ሀ. ተላላፊ በሽታ

ተላላፊ በሽታ ከበሽተኛው ሰው ወደ ጤነኛ ሰው በጥቃቅን ተሀዋስያን አማካኝነት የሚተላለፍ የበሽታ ዓይነት ነው።

**ምሳሌ፡-** ጉንፋን፣ የሳንባ ነቀርሳ፣ ኮሌራና የመሳሰሉት

## ለ. ተላላፊ ያልሆነ በሽታ

ይህ የበሽታ አይነት ደግሞ ከበሽተኛ ሰው ወደ ጤነኛ ሰው አይተላለፍም። በመሆኑም በበሽተኛው አካል ውስጥ በሚፈጠር ችግር የሚከሰት ነው።

**ምሳሌ፡-** የስኳር በሽታ፣ የጨጓራ በሽታ፣ የደም ግፊት፣ የደም ማነስና የመሳሰሉት ናቸው።


**ተማሪዎች!** ስለ በሽታ ስትማሩ ብዙ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ በሽታዎች እንዳሉ አትዘንጉ።

በዚህ ክፍል ስለ፡-

- ጉንፋን
- ወስፋት
- ወባ
- ተቅማጥና
- የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ መንስኤዎችና ስለሚያደርሱት ጉዳት ትማራላችሁ።

## 1. ጉንፋን

የጉንፋን በሽታ የሚከሰተው በቫይረስ አማካኝነት ነው። ቫይረሶች በጣም ጥቃቅንና በዓይን የማይታዩ ተሀዋስያን ናቸው። ጉንፋን የሚዛመተው በአየር ውስጥ ነው። በሽታው ከበሽተኛ ሰው ወደ ጤነኛ ሰው የሚተላለፈው በትንፋሽ፣ የመመገቢያ እቃዎችን በጋራ በመጠቀም፣ አፍንጫንና አፍን ሳይሸፍኑ በመሳልና በማስነጠስ ምክንያት ሊሆን ይችላል።



ሀ. ጉንፋን እንዳይተላለፍ የሚደረግ ጥንቃቄ ለ. በጉንፋን የተያዘ ሰው ጥንቃቄ የጉደለው አሳሳል

ሥዕል 1.11 የጉንፋን መተላለፊያ መንገድና እንዳይተላለፍ ሲደረግ የሚገባው ጥንቃቄ

- ተማሪዎች! የጉንፋን በሽታ ጉንፋን ከያዘው ሰው ወደ ጤነኛ ሰው እንዴት እንደሚተላለፍ ከስዕል 1.11 ተረዳችሁ?
- ጉንፋን የያዘው ሰው ምን ምን ምልክቶች ይታዩበታል? ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ::

ጉንፋን የያዘው ሰው የተለያዩ ምልክቶች ይታዩበታል::

- የራስ ምታት
- ማስነጠስ
- አክታ
- የንፍጥ መዝረክረክና የመሳሰሉት ምልክቶች ይታዩበታል::

ተማሪዎች! የጉንፋን በሽታ እንዳይዘን ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለብን?

የጉንፋን በሽታ የያዘው ሰው ካጋጠመን በሽታው እስከሚሻለው ድረስ

- ወደ ታመመው ሰው አለመቅረብ
- በአንድ የመመገቢያ ዕቃ አብሮ አለመመገብ
- በመኖሪያ ቤታችንም ሆነ በትምህርት ቤት ክፍሎች ውስጥ ተገቢው የአየር ዝውውር እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል::

ጉንፋን ከያዘን ደግሞ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይኖርብናል::

- በቂ እረፍት መውሰድ
- ፍራፍሬዎችን መመገብ
- ትኩስ መጠጦችን መጠጣትና ካልተሻለን ደግሞ ወደ ሐኪም ቤት ሄዶ መታከም
- በሽታው ወደ ሌላ ሰው እንዳይተላለፍ ስንስልና ስናስነጥስ መሀረብ መጠቀም

## 2. ወስፋት

**ተማሪዎች!** ስለ ወስፋት በሽታ ምን ታውቃላችሁ?

የወስፋት በሽታ እንዴት እንደሚመጣ የምታውቁትን ያህል ለመምህራችሁ ንገሩ::



ሀ. የተበከለ ውሃ



ለ. የወስፋት ትል

ሥዕል 1.12 ስተለያዩ በሽታዎች የሚያጋልጥ የተበከለ ውሃ

የወስፋት በሽታ በተለይ ህፃናትን በጣም የሚያጠቃው ለምን ይመስላችኋል? ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ::

ህፃናት በወስፋት በሽታ የሚጠቁት በተለያዩ ምክንያቶች ነው:: ለምሳሌ:-

- ባለማስተዋል የተበከለ ውሃ ስለሚጠጡና የተበከለ ምግብ ስለሚመገቡ
- የወስፋት እንቁላል የያዘ አፈር ነክተው እጃቸውን በሳሙና ሳይታጠቡ ስለሚመገቡ ሊሆን ይችላል::

የወስፋት ትል የወስፋት በሽታን የሚያስከትል ጥገኛ ትል ነው:: በወስፋት በሽታ የተጠቃ ሰው በሜዳ ላይ ቢፀዳዳ ዓይነ ምድሩ በተለያዩ መንገዶች ወደ ውኃ አካላት ገብቶ ብክለት ሊያስከትል ይችላል:: በመሆኑም በሽታው በተበከለ ውኃና ምግብ አማካኝነት ወደ ጤነኛ ሰው ይተላለፋል::

የወስፋት ትል ወደ ሰውነት ውስጥ ከገባ በኋላ በአንጀት ውስጥ ይራባል:: ከዚያም እንቁላሉ ከበሽተኛው አይነምድር /ሰገራ/ ጋር በመውጣት በተለያዩ መንገዶች ወደ ጤነኛ ሰው ይገባል::

### የወስፋት በሽታ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በወስፋት በሽታ የተያዘ ሰው ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ::

- የሰውነት መክሳት
- የምግብ ፍላጐት መቀነስ

- የድካም ስሜት
- ማቅለሽለሽና ምራቅ መትፋት

የወስፋት በሽታን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ::
የወስፋት በሽታ መከላከያ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው::

- የምንመገባቸውን ምግቦች መሸፈን
- ቤትና አካባቢን በንጽህና መያዝ
- ውሃን አፍልቶ መጠጣት
- ውሃን አክሞ /ውሃ አጋርን በመጨመር/ መጠቀም
- መፀዳጃ ቤቶችን መጠቀም

## 3. የወባ በሽታ

የወባ በሽታ ኘላዝሞዲየም በሚባል ጥገኛ ህዋስ አማካኝነት የሚመጣ በሽታ ነው:: ይህ በሽታ በወባ ትንኝ አማካኝነት ከበሽተኛ ሰው ወደ ጤነኛ ሰው ይተላለፋል::

**ተማሪዎች! የወባ በሽታ ምልክቶችን ታውቃላችሁ? ምን ምን ናቸው?**

በወባ የተያዘ ሰው የሚከተሉት ምልክቶች ይታዩበታል::

- ማንቀጥቀጥ
- ማቅለሽለሽ
- ትኩሳት
- ማላብ
- ከፍተኛ ራስ ምታት
- የምግብ ፍላጎት ማጣት

ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች ሲስተዋሉ በአስቸኳይ ወደ ሐኪም ቤት በመሄድ መታከም አስፈላጊ ነው::


**የወባ በሽታን እንዴት መከላከል እንችላለን? ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ::**

የወባ በሽታን ለመከላከል ከሚያስችሉ ዘዴዎች ዋና ዋናዎቹ:-

- የወባ ትንኝ መራቢያ የሆኑትን የውሃ አካላት ማድረቅ
- በመኖሪያ ክፍል ውስጥ ፍሊት መንፋት
- መኝታን በአጎበር መሸፈን ናቸው::



ስዕሉ ምንን ያሳያል?



ከስዕሉ ምን ትረዳላችሁ?

ሥዕል 1.13 የወባ መከላከያ መንገዶች

የወባ ትንኝ በአካባቢያችሁ ትገኛለች? ማታ ማታ ምን ዓይነት ድምፅ ታሰማለች? ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ::

## 4. ተቅማጥ

**ተማሪዎች!** ተቅማጥ በሽታ ይዟችሁ ያውቃል? በሽታው እንዴት የሚከሰት ይመስላችኋል?

የተቅማጥ በሽታ የተበከለ ውሃና ምግብ ስንመገብ የሚመጣ በሽታ ነው:: የተቅማጥ በሽታ በምን በምን መንገዶች እንደሚተላለፍ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ::

የተቅማጥ በሽታ በተለያዩ መንገዶች ይተላለፋል:: እነዚህም:-

- የተበከሉ ቁሳቁሶችን መጠቀም
- በተበከለ እጅ ምግብን መብላት
- የተበከለ ውሃን መጠጣት
- የተበከሉ አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን መመገብ ናቸው::

የዚህ በሽታ ምልክቶች ደግሞ፡-

- ራስ ምታት
- ቁርጠት
- ትኩሳት
- ድካም
- የምግብ ፍላጐት መቀነስ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ይህ በሽታ በወቅቱ ካልታከሙት እስከ ሞት ሊያደርስ የሚችል ነው፡፡

**የተቅማጥ በሽታን እንዴት መከላከል ይቻላል?**

በሽታውን ለመከላከል የሚያግዙ የተለያዩ ጥንቃቄዎችን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ምግብ ከመመገባችን በፊትና ከተመገብን በኋላ እጃችንን መታጠብ
- ውሃን አፍልተን መጠጣት
- የተበከሉ አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን አለመመገብ
- በተገኘው ቦታ አለመፀዳዳት
- ከመፀዳጃ ቤት መልስ እጃችንን መታጠብ
- ምግብ አቅራቢዎች እጃቸውን ሳይታጠቡ የሚሰጡንን ምግብ አለመመገብ

- በመፀዳጃ ቤት መጠቀም የተቅማጥ በሽታን ለመከላከል እንዴት ይጠቅማል? በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡



ሥዕል 1.14 መፀዳጃ ቤት

## 5. ኤድስ

**ተማሪዎች!** ኤድስ ምንድን ነው? የመተላለፊያ መንገዶቹን ታውቃላችሁ? ተወያይታችሁ መልሱን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡


የኤድስ በሽታ ኤች አይ ቪ በሚባል ቫይረስ አማካኝነት የሚከሰት ነው።

- ኤድስ የሚገድልና ፈዋሽ መድኃኒት የሌለው በሽታ ነው።
- ኤድስ ተላላፊ በሽታ ነው።
- በሽታው ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው በደም ንክኪ ነው።

ይህም ሊሆን የሚችለው

- አንድን የህክምና መርፌ ለብዙ ሰው በመጠቀም
- በበሽታው የተያዙ ሰዎች የተጠቀሙበትን ስለታምና ሹል ነገሮችን በመጠቀም
- በመድማት ላይ የሚገኙ ሰዎችን ደም በመንካት ነው።

1. ከዚህ በታች የቀረቡትን ስዕሎች ስም ጻፉ።
2. በእነዚህ ቁሳቁሶች አማካኝነት ኤች.አይ.ቪ እንዴት እንደሚተላለፍ በቡድን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ግለጹ።



ሀ ለ ሐ መ ሠ

ሥዕል 1.15 ስኤች.አይ.ቪ መተላለፍ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ቁሳቁሶች

የኤድስ በሽታን ለመከላከል ምን ምን ማድረግ ይኖርብናል?

ዋና ዋናዎቹ የመከላከያ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው።

- ህክምና ሲወሰድ አዲስ መርፌ መጠቀም
- ሌላ ሰው የተጠቀመበትን ስለታም ነገር አለመጠቀም
- ከማንኛውም የደም ንክኪ መራቅና የመሳሰሉት ናቸው።

## መልመጃ 1.7

ሀ. የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ።

1. ጉንፋን መድሃኒት ያልተገኘለት በሽታ ነው።
2. ተቅማጥ በአየር መበከል ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው።
3. የወባ በሽታ ዋና ምልክቱ ማንቀጥቀጥና ማላብ ነው።
4. ከመፀዳጃ ቤት ስንወጣ እጃችንን በሳሙናና በውሃ መታጠብ ያስፈልጋል።
5. የወስፋት በሽታ ንጽህናቸው ባልተጠበቀ ምግብና ውሃ አማካኝነት ይከሰታል።

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።

1. ተላላፊ በሽታ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ኤድስ ሐ. ወባ
   ለ. ጉንፋን መ. ከፍተኛ የደም ግፊት
2. የወስፋት በሽታ ምልክት ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ማስነጠስ ሐ. ማቅለሽለሽ
   ለ. ሆድ ቁርጠት መ. የምግብ ፍላጐት ማጣት
3. በትንፋሽ የሚተላለፍ በሽታ የትኛው ነው?
   ሀ. ወባ ለ. ጉንፋን ሐ. ወስፋት መ. ኤድስ
4. የተቅማጥ በሽታ ምልክት ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ቁርጠት ሐ. ሳል
   ለ. ድካም መ. የምግብ ፍላጐት መቀነስ
5. ከሚከተሉት ውስጥ በሰው አንጀት ውስጥ የሚራባው የትኛው ነው?
   ሀ. የወስፋት ትል ሐ. ኤች. አይ. ቪ
   ለ. የወባ ትንኝ መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

## 1.4 አምስቱ የስሜት አካላት

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦**

- አምስቱን የስሜት አካላት ስሞች ትጠቅሳላችሁ።
- የስሜት አካላትን ተግባራት ታስረዳላችሁ።
- የታወቁ የብርሃን ምንጮችን ትለያላችሁ።
- ቢያንስ ሰባት ቀለማትን ትለያላችሁ።
- የማየት ስሜትን በመጠቀም በተግባር ታሳያላችሁ።
- የታወቁ የድምፅ ምንጮችን ትለያላችሁ።
- የመስማት ስሜትን በመጠቀም በተግባር ታሳያላችሁ።
- የተለመዱ ነገሮችን ጣዕሞች ትገልፃላችሁ።
- የመቅመስ ስሜትን በመጠቀም በተግባር ታሳያላችሁ።
- የማሽተት ስሜትን በመጠቀም በተግባር ታሳያላችሁ።
- ዕቃዎችን (ነገሮችን) በመንካት ሻካራ ወይም ለስላሳ እንዲሁም ሞቃትና ቀዝቃዛ በማለት ትገልፃላችሁ።

**ቁልፍ ቃል**

- የስሜት አካላት


**ተማሪዎች! ስንት ዓይነት የስሜት አካላት አሉ? ስማቸውን መጥራት ትችላላችሁ?**

**የስሜት አካላት አምስት ዓይነቶች ሲሆኑ**

**እነርሱም፡-**

1. **አፍንጫ**
2. **ምላስ**
3. **ጆሮ**
4. **ዓይንና**
5. **ቆዳ ናቸው።**

**ከዚህ በታች የሚገኙትን ስዕሎች በደንብ ተመልከቱ። የእያንዳንዱን የስሜት አካል ተግባር ለመምህራችሁ ንገሩ።**



**አፍንጫ**



**ምላስ**



**ጆሮ**



**እጅ**



**ዓይን**

**ስዕል 1.16 የሰው የስሜት አካላት**

## 1. አፍንጫ

**ተማሪዎች አፍንጫ የተለያዩ ነገሮችን በማሽተት ለመለየት የምንጠቀምበት የስሜት አካል መሆኑን ተረዳችሁ?**

**አሁን ደግሞ የተለያየ ሽታ ያላቸውን ነገሮች ምሳሌዎች ለመምህራችሁ ንገሩ።**

- **መልካም መአዛና መጥፎ ሽታ ያላቸው ነገሮች በሽታቸው ይለያሉ።**

የሚከተሉትን ስዕሎች በደንብ ተመልክታችሁ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።




- በሥዕሉ የሚታየው ገንዳ ምን ይዟል?
- ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?
- ምን ዓይነት ሽታ የሚሰማቸው ይመስላችኋል?



- በሥዕሉ የሚታየው ቤት የምን ቤት ነው?
- ሰውየው ምን እየደረገ ነው?
- ምን ዓይነት ሽታ የሸተተው ይመስላችኋል?



- ልጁ ምን እየደረገ ነው? ምን ዓይነት ሽታ የሚሰማው ይመስላችኋል?




- ልጅቷ ምን እያደረገች ነው?
- ምን ዓይነት ሽታ የሚሰማት ይመስላችኋል?

ሥዕል 1.17 የተለያዩ ሽታዎች ሲሰዩ

**ተማሪዎች!** ከስዕሎቹ ምን ተገነዘባችሁ? ጥሩ ሽታና መጥፎ ሽታ ያላቸውን ነገሮች በአፍንጫችን መለየት እንደምንችል ተረዳችሁ::

**ተማሪዎች!** ሌላው መገንዘብ ያለባችሁ ጉዳይ ደግሞ በሽታ ብቻ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮች መኖራቸውን ነው:: ስለሆነም የምናሽተው ነገር ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ሳናረጋግጥ ማሽተት የለብንም ማለት ነው::

## መልመጃ 1.8

**የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ::**

1. መፀዳጃ ቤት በንጽሕና ካልተያዘ መጥፎ ሽታ ያመጣል::
2. ሽቶ ጥሩ መዓዛ አለው::
3. አበባ ጥሩ መዓዛ የለውም::

## 2. ምላስ

**ተማሪዎች!** ምላስ ነገሮችን ለመቅመስ የምንጠቀምበት የስሜት አካል ነው:: በመቅመስ የሚለዩ የጣዕም ዓይነቶችን ለመምህራችሁ ንገሩ::

በምላሳችን በመቅመስ የምንለያቸው የጣዕም ዓይነቶች:-

- ጣፋጭ
- መራራ
- ኮምጣጣና
- ጨዋማ ናቸው::

**የሚከተሉትን ሥዕሎች በደንብ አስተውሉ::**



ሙዝ ምን ዓይነት ጣዕም አለው?



የሎሚ ጣዕም ምን ዓይነት ነው?



ግራዋ ምን ዓይነት ጣዕም አለው?

ሥዕል 1.18 የተለያየ ጣዕም ያላቸው ነገሮች

**ተማሪዎች!** ሙዝ ጣፋጭ ጣዕም እንዳለው፣ ሎሚ ኮምጣጣ መሆኑንና ግራዋ ደግሞ መራራ እንደሆነ ተገንዝባችኋል? የማናውቃቸውን ነገሮች ሁሉ መቅመስ ተገቢ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? አንድን ነገር በመቅመስ የምንለየው ጉጂ ወይም መርዛማ ስለአለመሆኑ እርግጠኞች ስንሆን ብቻ ነው።

## መልመጃ 1.9

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. ንፁህ ውኃ ጣዕም አለው?
2. ሎሚ ምን ዓይነት ጣዕም አለው?
3. የማር ጣዕም ምን ዓይነት ነው?
4. ጉመን ምን ዓይነት ቀለም አለው?
5. የቲማቲም ቀለም ምን አይነት ነው?

**ለ. በ«ሀ» ሥር የሚገኙትን የተለያየ ጣዕም ያላቸውን ነገሮች በ«ለ» ሥር ከቀረቡት የጣዕም ዓይነቶች ጋር በመስመር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ስኳር | መራራ |
| 2. ሎሚ | ጣፋጭ |
| 3. ግራዋ | ኮምጣጣ |


## 3. ጆሮ

**ተማሪዎች!** ጆሮ ለምን እንደሚጠቅም ለመምህራችሁ ንገሩ። በመስማት የተለያዩ ድምጾችን መለየት እንችላለን።

በአካባቢያችሁ የምን የምን ድምፅ ትሰማላችሁ? ከእናንተ መካከል የአንዳንድ እንስሳትን ድምፅ ሊያሰሙ የሚችሉ ተማሪዎች አሉ? እጅ በማውጣት መምህራችሁ ሲፈቅዱላችሁ በየተራ ሞክሩ።

**የቤት እንስሳትን ድምፃች በመስማት መለየት**

ከዚህ በታች በሚገኘው ሰንጠረዥ ውስጥ የምትመለከቷቸውን እንስሳት ድምፃቸውን በመለየት በተገቢው ቦታ ፃፉ። (አንድ ምሳሌ ተሰርቶላችኋል)።

| ተ.ቁ | የእንስሳው ስዕል | የሚያሰማው ድምፅ |
|---|---|---|
| 1 |  | ኩኩሉ |
| 2 |  | |
| 3 |  | |
| 4 |  | |
| 5 |  | |
| 6 |  | |

## መልመጃ 1.10

በ«ሀ» ሥር የቀረቡትን የድምፅ ዓይነቶች በ«ለ» ሥር ከቀረቡት የእንስሳት ስም ጋር በመስመር በማገናኘት አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. በአ በአ | ዶሮ |
| 2. ሚያው | ውሻ |
| 3. ኩኩሉ | ላም |
| 4. ውውው | በግ |
| 5. እምቧ | ድመት |

### የዱር እንስሳት ድምፅ

ከዚህ በታች ያሉት የዱር እንስሳት ምን ዓይነት ድምፅ ያሰማሉ? የዱር እንስሳቱን ድምፅ አስመስላችሁ ለመምህራችሁ አሰሙ።



የወፍ ጫጫታ

ወፍ ምን ዓይነት ድምፅ ታሰማለች?



የጅብ ጩኸት

የጅብ ድምፅ ምን ዓይነት ነው?



የአንበሳ ግሳት

አንበሳ ምን ዓይነት ድምፅ ያሰማል?

ስ ዕል 1.19 የተለያዩ ድምፅ የሚያሰሙ የዱር እንስሳት

### የሞተር ድምፅ

ከዚህ በታች በስዕሉ ላይ የተገለፀው እያንዳንዱ የመጓጓዣ ዓይነት ምን ዓይነት ድምፅ አለው?



መኪና




አውሮፕላን

ስዕል 1.20 የተለያዩ ድምፅ የሚያሰሙ የመጓጓዣ ዓይነቶች

## የሙዚቃ መሣሪያ ድምፅ

**ተማሪዎች! የምታውቋቸውን የሙዚቃ መሣሪያዎች የድምፅ ዓይነቶች ለመምህራችሁ ተናገሩ::**


ክራር


ዋሽንት


ከበሮ


ማሲንቆ


በገና

**ሥዕል 1.21 ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች**


ሳክስፎን


ጊታር

**ስዕል 1.22 ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች**

## መልመጃ 1.11

**በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን የድምፅ ዓይነቶች ከዚህ በታች በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ፃፉ::**


1. _____
2. _____
3. _____
4. _____

## የሰዎችን ሁኔታ የሚገልፁ የድምፅ ዓይነቶች

ከዚህ በታች በስዕሉ ላይ ከሚታዩት ሰዎች ምን ምን ዓይነት ድምፅ እንደሚወጣ ለመምህራችሁ ለማሰማት ሞክሩ::



ህፃኑ ሲስቅ



መምህሩ ሲመክረ



የሰዎች ኡኡታ

ሥዕል 1.23 የተለያዩ የድምፅ ዓይነት መገለጫዎች

### 4. ዓይን

ተማሪዎች! ባለፈው ትምህርታችሁ ዓይን በአካባቢያችን የሚገኙትን ነገሮች ለማየት የምንጠቀምበት የአካል ክፍል መሆኑን ተምራችኋል::

ምን ምን ነገሮችን በማየት መለየት እንችላለን? ምሳሌ ስጡ::

የብርሃን ምንጮችን በማየት መለየት እንችላለን:: በአካባቢያችን የተለያዩ የብርሃን ምንጮች ይገኛሉ:: ለምሳሌ:- ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ በመብራት ላይ የሚገኝ አምፑል፣ ሻማ፣ ኩራዝ፣ ፋኖስና ባትሪ ዋና ዋናዎቹ ናቸው::


የሚከተሉትን ሥዕሎች ተመልክታችሁ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።



- በስዕሉ የሚታየው የብርሃን ምንጭ ምንድን ነው?
- ከዚህ የብርሃን ምንጭ ብርሃን የሚታየው ምን ጊዜ ነው?



- ስዕሉ የትኛውን የብርሃን ምንጭ ያሳያል?
- ይህ ብርሃን የሚታየው ምን ጊዜ ነው?



- በስዕሉ ላይ የሚታየው የብርሃን ምንጭ ምንድን ነው?
- የምናበራው ምን ጊዜ ነው?




- በስዕሉ የሚታየው ሰው የያዘው የብርሃን ምንጭ ምን ይባላል?
- በብርሃን ምንጭነት የምንጠቀምበት ምን ጊዜ ነው?



- በስዕሉ ላይ የሚታዩት ሰዎች ምን እያደረጉ ይመስላችኋል?
- በስዕሉ የሚታየው የብርሃን ምንጭስ ምንድን ነው?
- ይህ የብርሃን ምንጭ ለምን ለምን እንደሚያገለግል ግለጹ።



- በስዕሉ በጐጆ ቤቱ ውስጥ የሚታየው የብርሃን ምንጭ ምንድን ነው?
- አገልግሎት የሚሰጠው ምን ጊዜ ነው?



- በስዕሉ ላይ የምታዩት የብርሃን ምንጭ ምንድን ነው?
- በብርሃን ምንጭነት የሚያገለግለው ምን ጊዜ ነው?

ሥዕል 1.24 የተለያዩ የብርሃን ምንጮች

**ተማሪዎች! የብርሃን ምንጮች በስንት እንደሚመደቡ ታውቃላችሁ?**

የብርሃን ምንጮች በሁለት ይመደባሉ። እነርሱም

- በተፈጥሮ የሚገኙ የብርሃን ምንጮችና
- ሰው ሰራሽ የብርሃን ምንጮች ናቸው።

በስዕል 1.24 ከቀረቡት የብርሃን ምንጮች ውስጥ የትኞቹ ተፈጥሯዊ የትኞቹ ደግሞ ሰው ሰራሽ እንደሆኑ ለመምህራችሁ ግለጹ።

## መልመጃ 1.12

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. በቀን ብርሃንን የምናገኘው ከምንድን ነው?
   ሀ. ከጨረቃ ለ. ከፀሐይ ሐ. ከኩራዝ
2. ከሚከተሉት ውስጥ የተፈጥሮ ብርሃን ሰጭ የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ፋኖስ ለ. ሻማ ሐ. ጨረቃ
3. የተለያዩ ነገሮችን ለማየት የሚጠቅመን የአካላችን ክፍል የትኛው ነው?
   ሀ. ዓይን ለ. አፍንጫ ሐ. ጆሮ

## 5. ቆዳ

**ተማሪዎች! የነገሮችን ሻካራነትና ልስላሴ እንዴት እንለያለን?**

ቆዳ ውስጣዊ አካላችንን የሚሸፍን የሰውነት ክፍል ነው፡፡ የተለያዩ ነገሮችን ሻካራነትና ልስላሴ በጣቶቻችን በመዳሰስ መለየት እንችላለን፡፡

ሞቃትና ቀዝቃዛ ነገሮች በእጆቻችን አማካኝነት ሊለዩ ይችላሉ፡፡

- የጣት ቆዳችንን ለመዳሰስ እንጠቀማለን፡፡

**ተማሪዎች!** የለስላሳና የሻካራ ነገሮችን ምሳሌዎች መስጠት ትችላላችሁ?

**ለስላሳ ነገሮች የሚባሉት፡-** ጥጥ፣ ወረቀት፣ ላስቲክ

**ሻካራ ነገሮች፡-** እንጨት፣ አሸዋ፣ አፈር

**ተማሪዎች!** የራሳችሁን ልብስ ነክታችሁ ሻካራነቱንና ልስላሴውን በመለየት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡



ጂንስ ሱሪ ሸካራ ነው



ሸሚዝ ለስላሳ ነው



ቆዳ ጃኬት ለስላሳ ነው



የክር ሹራብ ሸካራ ነው

ሥዕል 1.25 በመዳሰስ ሊለዩ የሚችሉ የልብስ ዓይነቶች



- በስዕሉ የሚታየው ልጅ ዓይኑ እንደተሸፈነ በእጆቹ በመዳሰስ ብቻ የያዘው ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ የሚችል ይመስላችኋል?

ስዕል 1.26 ልጁ ዓይኑ እንደተሸፈነ በጠረጴዛ ላይ የተቀመጠለትን ነገር ሲዳስስ

## መልመጃ 1.13

**ሀ. የሚከተሉትን ነገሮች «ስስሳሳ» ወይም «ሻካራ» በማለት ለይታችሁ ጻፉ::**

1. ወረቀት _____
2. ወለል _____
3. ጫማ _____
4. መስታዎት _____
5. አሸዋ _____
6. ጥጥ _____
7. አፈር _____

**ለ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ::**

1. ብርሃን ነገሮችን ለማየት አስፈላጊ ነው::
2. ግራዋ ጣፋጭ ጣዕም አለው::
3. ውሃንና አምቦ ውሃን በጣዕማቸው መለየት ይቻላል::
4. ማር ኮምጣጣ ነው::

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ::**

1. ስኳርና ጨውን በምን እንለያለን?
   ሀ. በቀለማቸው ለ. በሽታቸው ሐ. በጣዕማቸው
2. ለማሽተት የምንጠቀምበት የስሜት አካል የትኛው ነው?
   ሀ. ዓይን ለ. አፍንጫ ሐ. ጆሮ
3. ከሚከተሉት ውስጥ የላምን ድምፅ የሚወክለው የትኛው ነው?
   ሀ. ዉዉዉ ለ. እምቢ እምቢ ሐ. ባአ ባአ
4. የስልክ መልዕክት የምንቀበለው በየትኛው የስሜት አካል ነው?
   ሀ. በዓይን ለ. በአፍንጫ ሐ. በጆሮ

# ማጠቃለያ

- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች የሚባሉት ራስ፣ ጆሮ፣ ዓይን፣ አፍንጫ፣ አፍ፣ እጅ፣ ጣት፣ አንገት፣ ደረት፣ ትከሻ፣ ሆድ፣ ወገብ፣ ቅልጥም፣ ጉልበትና እግር ናቸው።
- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች እንደ የቅርጻቸውና እንደ አቀማመጣቸው ተግባራቸውም ይለያያል።
- ውጫዊ የሰውነት ክፍሎች ተግባራቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ንፅህናቸው መጠበቅ አለበት።
- የሰው ልጅ ሶስቱ መሠረታዊ ፍላጐቶች ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ናቸው።
- ምግብ ለሰው ልጆች አካላዊ ዕድገት፣ ጥንካሬና ጉልበት በጣም ጠቃሚ ነው።
- አልባሳት ከፀሐይ ብርሃን፣ ከቅዝቃዜ፣ ከብርድ፣ ከዝናብና ከመሳሰሉት ለመከላከል እንዲሁም ገላን ለመሸፈንና ለውበት ይጠቅማሉ።
- አልባሳት ከጥጥ፣ ከሱፍ፣ ከቆዳና ከናይለን ሊሠሩ ይችላሉ።
- መጠለያ ከዝቅቃዜ፣ ከፀሐይ ብርሃን፣ ከዝናብ፣ ከነፋስና ከአደገኛ የዱር እንስሳት ለመከላከል ይጠቅማል።
- መጠለያዎች ከሣር፣ ከእንጨት፣ ከጠፍጣፋ ብረት፣ ከሸክላ፣ ከጭቃ፣ ከሲሚንቶና ከአሸዋ ሊሠሩ ይችላሉ።
- በህፃናት ላይ ከሚከሰቱ በሽታዎች ውስጥ በዋናነት የሚታወቁት ጉንፋን፣ ወስፋት፣ ወባና ተቅማጥ ናቸው።
- ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ በደም አማካኝነት የሚተላለፍ በሽታ ነው። ስለሆነም ከማንኛውም የሰው ደም ንክኪና በደም ከተበከሉ ሹል ነገሮች መራቅ ያስፈልጋል።
- ኤድስ የሚገድልና መድኃኒት የሌለው በሽታ ነው።
- ጉንፋን በአየር አማካኝነት የሚተላለፍ በሽታ ነው።
- የወስፋት በሽታ በሰው እዳሪ አማካኝነት ይዛመታል። ይኸውም በተበከለ ውሃና በተበከለ ምግብ ወደ ጤነኛ ሰው በመግባት በአንጀት ውስጥ ይራባል።
- የወባ በሽታ ኘላዝሞዲየም በሚባል ጥገኛ ህዋስ አማካኝነት የሚመጣ በሽታ ነው። በሽታው በወባ ትንኝ አማካኝነት ከበሽተኛ ወደ ጤነኛ ሰው ይተላለፋል።
- የተቅማጥ በሽታ በአሜባና በባክቴሪያ አማካኝነት ይከሰታል።
- ዓይን፣ ጆሮ፣ ምላስ፣ አፍንጫ፣ ቆዳ አምስቱ የስሜት አካላት ናቸው።
- ዓይናችን የተለያዩ ነገሮችን በማየት የምንለይበት የስሜት አካል ነው።
- ማንኛውንም ነገር ለማየት ብርሃን አስፈላጊ ነው። የብርሃን ምንጮች፡- ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ሻማ፣ ባትሪ፣ ኩራዝ፣ የኤሌክትሪክ ብርሃን ወዘተ... ናቸው።

- ዓይናችን የተለያዩ ቀለማትን ለመለየት ይጠቅማል፡፡
- ጆሮ ለመስማት የምንገለገልበት የስሜት አካላችን ነው፡፡
- በጆሮአችን የተለያዩ ድምፆችን እንሰማለን፡፡ የሰማናቸውን ድምፆችም የምን የምን ነገሮች እንደሆኑ መለየት እንችላለን፡፡
- ምላስ የተለያዩ ነገሮችን ለመቅመስ የምንገለገልበት የስሜት አካላችን ነው፡፡
- በምላሳችን ጣፋጭ፣ መራራ፣ ኮምጣጣና ጨዋማ ጣዕሞችን እንለያለን፡፡
- በአፍንጫችን ጥሩና መጥፎ ሽታ ያላቸውን ነገሮች እንለያለን፡፡
- ቆዳ ለመዳሰስ የምንጠቀምበት የስሜት አካላችን ነው፡፡ በእጃችን ቆዳ አማካኝነት ሻካራና ለስላሳ ነገሮችን እንዲሁም ሞቃትና ቀዝቃዛ ነገሮችን እንለያለን፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ወረፋተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ።**

1. ጽጌረዳ ጥሩ ሽታ አለው።
2. ቀለማትን በመዳሰስ መለየት እንችላለን።
3. ሳቅ የደስታ መግለጫ ነው።
4. የሙዚቃ መሣሪያዎች ሁሉ አንድ ዓይነት ድምፅ አላቸው።
5. ከምላስ በስተቀር ሁሉም የስሜት አካላት ውጫዊ ናቸው።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።**

1. ብርሃን አመንጭ ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ሻማ ለ. ኩራዝ ሐ. መስታዎት

2. ከሚከተሉት ውስጥ በአየር አማካኝነት የሚተላለፈው በሽታ የትኛው ነው?

   ሀ. ጉንፋን ለ. ተቅማጥ ሐ. ወስፋት

3. ቴሌቪዥን ስንከታተል የትኞቹን የስሜት አካላት እንጠቀማለን?

   ሀ. ዓይንና አፍንጫ ለ. ጆሮና ቆዳ ሐ. ዓይንና ጆሮ

4. መሠረታዊ ፍላጐት ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ቤት ለ. መኪና ሐ. ልብስ

5. ጣዕሞችን በምን እንለያለን?

   ሀ. በዓይናችን ለ. በምላሳችን ሐ. በእጃችን

**ሐ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ስንት ዓይነት ቀለም አለው?
2. የስሜት አካላት የሚባሉት እነማን ናቸው?
3. ሶስት የሰዎችን ስሜት የሚገልጹ የድምፅ ዓይነቶች የሚፈጠሩባቸውን ሁኔታዎች ጻፉ።
4. የሰው መሠረታዊ ፍላጐቶች ስንት ናቸው? ስማቸውን ጻፉ።
5. የተለያዩ ቀለማትን በምን እንለያለን?

## ፍተሻ

*ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሳጥኖች ውስጥ በማስቀመጥ አመልክቱ።*

1. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቼን ስሞች እጠቅሳለሁ። ☐
2. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቼን በመንካት አሳያለሁ። ☐
3. ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቼን ተግባራት እናገራለሁ። ☐
4. ሦስቱን መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጐቶች እዘረዝራለሁ። ☐
5. ስለሦስቱ መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጐቶች ጥቅሞች አስረዳለሁ። ☐
6. ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉትን የታወቁ በሽታዎችን ስሞች እጠቅሳለሁ። ☐
7. የታወቁ በሽታዎችን ለማስወገድ የሚረዱ ቅድመ ጥንቃቄዎችን እገልጻለሁ። ☐
8. አምስቱን የስሜት አካላት ስሞች እጠቅሳለሁ። ☐
9. የስሜት አካላትን ተግባራት አስረዳለሁ። ☐
10. የታወቁ የብርሃን ምንጮችን እለያለሁ። ☐
11. ሰባቱን የቀለም ዓይነቶች እለያለሁ። ☐
12. የማየት ስሜትን በመጠቀም በተግባር አሳያለሁ። ☐
13. የታወቁ የድምፅ ምንጮችን እለያለሁ። ☐
14. የመስማት ስሜትን በመጠቀም በተግባር አሳያለሁ። ☐
15. የተለመዱ ነገሮችን ጣዕሞች እገልፃለሁ። ☐
16. የመቅመስ ስሜትን በመጠቀም በተግባር አሳያለሁ። ☐
17. የማሽተት ስሜትን በመጠቀም በተግባር አሳያለሁ። ☐
18. ዕቃዎችን (ነገሮችን) በመንካት ሻካራ ወይም ለስላሳ እንዲሁም ሞቃትና ቀዝቃዛ በማለት እለያለሁ። ☐

# ምዕራፍ ሁለት

# ቤተሰባችን

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የቤተሰቦቻችሁን አባላት በመዘርዘር የሥራቸውን ዓይነት ትናገራላችሁ፡፡
- የምትመገቡት ምግብ ምንጭ ግብርና መሆኑን ትጠቅሳላችሁ፣ በቤታችሁ የሚገኙ ሰብሎችና የሰብል ውጤቶች ስሞች ትጠራላችሁ፣ ሰብሎችን ትንከባከባላችሁ፡፡
- አልባሳትና መጠለያዎች ከምን ከምን እንደተሠሩ ታሳያላችሁ፣ የተለያዩ አልባሳትንና መጠለያዎችን ትለያላችሁ፡፡
- አንዳንድ የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ስሞች ትጠቅሳላችሁ፣ ጥቅማቸውንና በምን እንደተሠሩ በመናገር በጥንቃቄ ትይዛላችሁ፡፡
- ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎቶችን ማለትም፡- መመልከትን፣ መጠየቅን፣ መግባባትን፣ ተባብሮ መሥራትንና መመደብን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦<br>• የቤተሰቦቻችሁን አባላት ስም ትዘረዝራላችሁ።<br>• የቤተሰቦቻችሁን አባላት ሥራ ትገልፃላችሁ።<br>• ሌሎች የቤተሰብ አባላትን ለመርዳት ዝግጁነትን፣ ደግነትንና የኃላፊነት ስሜትን በተግባር ታሳያላችሁ። |

**ቁልፍ ቃላት**

- ቤተሰብ
- የቤተሰብ ተግባራት

## 2.1 የቤተሰብ አባላት


### ሀ. የቤተሰብ አባላት ዝርዝርና ግንኙነት

- ተማሪዎች የቤተሰብ አባላት የሚባሉት እነማን እንደሆኑ ታውቃላችሁ?
- የናንተ የቤተሰብ አባላት ብዛት ስንት እንደሆነ ተራ በተራ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

➢ የቤተሰብ አባላት የሚባሉት፦

- ✓ አባት
- ✓ እናት
- ✓ ልጆች እና
- ✓ ሌሎች

ተማሪዎች! ከዚህ በታች የቀረበውን ስዕል ተመልከቱ



ሥዕል 2.1 የአንድ ቤተሰብ አባላት

**ስዕሉ 2.1ን በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::**

1. የዚህ ቤተሰብ አባላት ብዛት ስንት ነው?
2. በቤተሰቡ ውስጥ ስንት ልጆች አሉ?

**ተማሪዎች! ለታላላቆቻችሁና ለቤተ ዘመዶቻችሁ ምን ምን በማድረግ አክብሮት እንደምታሳዩ በቡድን በቡድን ሆናችሁ በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::**

በቤተሰብ፣ በልጆችና በቤተዘመድ መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት በሚከተሉት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት::

ሀ. መተሳሰብ
ለ. መግባባት
ሐ. መፈቃቀር
መ. መከባበር
ሠ. በሥራ መረዳዳት
ረ. ችግርን በጋራ መፍታት
ሰ. ታማኝነት

**ተማሪዎች! ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች ተመልከቱ::**

**ሰዎቹ ምን እያደረጉ ነው? እናንተስ ከቤተሰባችሁ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት አላችሁ? እስቲ ተወያዩ**

**ሀ)**




**ለ)**



**ሐ)**



**መ)**



**ሥዕል 2.2 የቤተሰብ አባላት የተለያዩ ስራዎችን ሲያከናውኑ**

## መልመጃ 2.1

**ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ #እውነት; ትክክል ካልሆኑ ደግሞ #ሐሰት; በማለት መልሱ።**

1. በቤተሰብ መካከል መፈቃቀር አስፈላጊ ነው።
2. ታማኝነት ቤተሰባዊ ሥነ-ምግባር አይደለም።
3. ልጆች ወላጆቻቸውን በስራ ማገዝ አለባቸው።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።**

1. ቤተሰባዊ መከባበር ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. መረዳዳት ሐ. መጨቃጨቅ

ለ. መግባባት መ. መፈቃቀር

2. በታላላቆችና በታናናሽ ልጆች መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት መኖር አለበት?

ሀ. መከባበር ሐ. መግባባት

ለ. መተሳሰብ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

**ሐ. የቤተሰብ አባላት በቤተሰብ ውስጥ ምን ድርሻ አላቸው?**

**ተማሪዎች!** ወላጆቻችሁ እንደቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸው ምን ምን ያደርጋሉ? ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያያት መልሶቹን ለመምህራችሁ ንገሩ:

**እስቲ ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች ተመልከቱ**




እናት በአግባቡ ልጆቿን ለማሳደግ ጠንክራ ትሠራለች



አባት የቤተሰቡን ህይወት በአግባቡ ለመምራት ጥረት ያደርጋል



እናት ለልጇ የተመጣጠነ ምግብ ስትመግበው



አባት ልጆችን ሲያስጠና

ሥዕል 2.3 የወላጆች የሥራ ድርሻ

ተማሪዎች! ከዚህ በታች ባለው ሥዕል የልጆችን የሥራ ድርሻ ተመልከቱ

ሀ)



ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ምን እያደረጉ ነው?

ለ)



ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?

ሐ)



ልጁ ምን እያደረገ ነው?

መ)



ልጆቹ ምን በማድረግ ላይ ናቸው?


ሥዕል 2.4 የልጆች የሥራ ድርሻ

**ተማሪዎች!** በቤታችሁ የእናንተ የሥራ ድርሻዎች ምን ምን ናቸው? መልሶቻችሁን ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩና ለመምህራችሁ ንገሩ::

**የልጆች የሥራ ድርሻ**

1. ደንብንና ሥነ-ሥርዓትን ማክበር፣
2. መታዘዝ፣
3. ቤተሰብን በሥራ መርዳት ናቸው::

**ተማሪዎች!** ቀጥሎ የተቀመጡትን ሥዕሎች አስተውሉ:: ወላጆች በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተሰማርተው ሲሰሩ ይታያሉ::



ነጋዴ



ሐኪም



ትራፊክ ፖሊስ



ዶሮ ማርባት



ምግብ ማብሰል

ሥዕል 2.5 በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሰማሩ የቤተሰብ አባላት

**መወያያ ጥያቄዎች**

- በአካባቢያችሁ በጣም የተለመደው የትኛው የሥራ ዓይነት ነው?
- **ተማሪዎች!** ትምህርታችሁን ስትጨርሱ በየትኛው የሥራ መስክ መሰማራት ትፈልጋላችሁ? ለምን መረጣችሁት?

## መልመጃ 2.2

**የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሥራ ድርሻ አለው።
2. የአባት ሥራ ምግብ ማብሰል ብቻ ነው።
3. የልጆች የሥራ ድርሻ መጫወት ብቻ ነው።

**ሐ. ከሌሎች የቤተሰብ አባላት ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር**

- **ተማሪዎች! ሌሎች የቤተሰብ አባላት የሚባሉት እነማን ናቸው?**
- **ከእነርሱስ ጋር እንዴት መልካም ግንኙነት መፍጠር ይቻላል? ተወያይታችሁ መልሶቹን ለመምህራችሁ ተናገሩ።**


**ተማሪዎች! ከዚህ በታች የቀረቡትን ሥዕሎች ተመልከቱ**



ልጆች ከአያቶቻቸው ምክር ሲቀበሉ




ልጆች ልደት ሲያከብሩ



ልጆች በንደኛቸው ምረቃ ሲሳተፉ





ልጆች ቤተሰቦቻቸውን በሥራ ሲረዱ

**ሥዕል 2.6 በቤተሰብ አባላት መካከል የሚደረግ መልካም ግንኙነት**

## መልመጃ 2.3

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. የአባት ወንድም ምን ይባላል?
2. አያት ማለት ምን ማለት ነው?
3. ከሌሎች የቤተሰብ አባላት ጋር እንዴት መልካም ግንኙነት መፍጠር ይቻላል?

## 2.2. ለቤተሰባችን፣ ምግብ፣ መጠለያና፣ ልብስ ያስፈልጋል

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ግብርና የምግብ ምንጭ መሆኑን ትረዳላችሁ፡፡
- በቤቶቻችሁ ውስጥ የሚገኙትን የእህል ዓይነቶችና ስሞቻቸውን ትጠራላችሁ::
- የተለያዩ የልብስ ዓይነቶችን ትለያላችሁ::
- ልብስን ለመሥራት የሚያገለግሉ የቁሳቁሶችን ስሞች ትጠቅሳላችሁ፡፡

**ቁልፍ ቃላት**

- ምግብ
- መጠለያ
- ልብስ

### 1. ምግብ

**ተማሪዎች!** በአካባቢያችሁ የሚገኙ የግብርና ውጤቶች ምን ምን ናቸው? ከጓዳኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሶቻችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

**ግብርና የምግብ ምንጭ መሆኑን ታውቃላችሁ? ከግብርና ለምግብ ምንጭነት የሚያገለግሉ የተለያዩ ውጤቶች ይገኛሉ፡፡**

የሚከተሉትን ስዕሎች በትኩረት ተመልከቱ፡፡


ስንዴ


በቆሎ


ባቄላ


ሽንብራ


ጤፍ


ፍራፍሬ


ሥጋ


ወተት


እንቁላል


አትክልት

ሥዕል 2.7 ለምግብነት የሚውሉ የተለያዩ የግብርና ውጤቶች

ተማሪዎች! ከላይ ከተጠቀሱት የግብርና ውጤቶች ምን ምን ዓይነት ምግቦችን ማዘጋጀት ይቻላል? ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች በደንብ ተመልከቱ፡፡


ከጤፍ የተዘጋጀ አንጀራ


ከስንዴ የተዘጋጀ ፓስታ


ከአተር ሽሮ የተሠራ ወጥ


ከገብስ የተዘጋጀ ቆሎ


የበቆሎ ጥብስ


ለጭማቂ የሚውሉ ፍራፍሬዎች


የብርቱካን ጭማቂ

ሥዕል 2.8 ከተለያዩ የእህል ዘሮችና ፍራፍሬዎች የተዘጋጁ የምግብ ዓይነቶች

## መልመጃ 2.4

**የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።።**

1. ዳቦ ከአተር ሊዘጋጅ ይችላል።
2. ጤፍ ከእህል ዘሮች አይመደብም።
3. ማሽላ ወጥ ለመስራት ይጠቅማል።

## 2. ልብስ

**ተማሪዎች!** እስቲ የምታውቋቸውን የልብስ ዓይነቶች ዘርዝሩ። ልብሶች ከምን ከምን እንደሚሠሩ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ።

### የአልባሳት ዓይነቶች

**ተማሪዎች!** ከዚህ በታች የቀረቡትን ሥዕሎች በመመልከት ልዩነታቸውን አስረዱ።



**ሥዕል 2.9 የተለያዩ የልብስ ዓይነቶች**

### አልባሳትን ለመሥራት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች

**ተማሪዎች!** ልብሶች ከምን ከምን ይሠራሉ? በአካባቢያችሁ የሚዘጋጁ የልብስ ዓይነቶችን ዘርዝሩ።

**የሚከተሉት ሥዕሎች የተለያዩ የልብስ መሥሪያ ጥሬ ዕቃዎችን ያመለክታሉ። በትኩረት ተመልከቱ። የትኞቹ የልብስ መሥሪያ ጥሬ ዕቃዎች በአካባቢያችሁ ይገኛሉ?**



ጥጥ



ሐር



የበግ ፀጉር (ሱፍ)



ቆዳ

ሥዕል 2.10 የተለያዩ የልብስ መሥሪያ ጥሬ እቃዎች

ልብስ ከተለያዩ ነገሮች ሊሠራ ይችላል። በዋናነት ልብስ ከጥጥ፣ ከቆዳ፣ ከበግ ፀጉር (ሱፍ)፣ ከሐር፣ ከናይሎንና ከመሳሰሉት ነገሮች ይሠራል።

## ሰንጠረዥ 2.1 የልብስ ዓይነቶችና የሚሠሩባቸው ቁሳቁሶች

| ተ.ቁ | የልብስ መሥሪያ ጥሬ ዕቃ | ከጥሬ ዕቃው የሚሠሩ የልብስ ዓይነቶች |
|---|---|---|
| 1. | ጥጥ | ነጠላ፣ ጋቢ፣ ሸሚዝ፣ ጂንስ ሱሪ፣ የባህል ልብስ፣ ካናቴራ፣ ጨርቅ ሱሪ/ካኪ/ |
| 2. | ቆዳ | ጃኬት፣ ጫማ፣ ቀበቶ፣ ጓንት |
| 3. | የበግ ፀጉር /ሱፍ/ | የወንድ ሙሉ ልብስ፣ የሴት ሙሉ ልብስ፣ ብርድ ልብስ፣ ሹራብ |
| 4. | ሐር | የራት ልብስ፣ ሻርፕ፣ ሸሚዝ |
| 5. | ናይሎን | ሹራብ፣ ሸሚዝ |

## መልመጃ 2.5

የሚከተሉትን ሥዕሎች አስተውላችሁ ተመልከቱ:: በመቀጠልም በ#ሀ; ረድፍ የሚገኙትን የልብስ ዓይነቶች በ"ለ" ረድፍ ከሚገኙት የልብስ መሥሪያ ጥሬ ዕቃዎች ጋር በማስመር አዛምዱ::

| 'ሀ' | | 'ለ' | |
|---|---|---|---|
| 1. |  | ሀ. |  |
| 2. |  | ለ. |  |
| 3. |  | ሐ. |  |
| 4. |  | መ. |  |

## 3. መጠለያ

**ተማሪዎች!** መጠለያ ምንድን ነው? መጠለያ ለምን ይጠቅማል? ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ::

የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ምን እንደተገነዘባችሁ ለመምህራችሁ ግለፁ።



ፎቅ ቤት



ቪላ ቤት



የጋራ መኖሪያ ሕንጻዎች



የሣር ክዳን ቤት

ስዕል 2.11 የተለያዩ የመጠለያ ዓይነቶች

መጠለያ ማለት የምንኖርበት ቤት ማለት ነው። መጠለያ ከዝናብ፣ ከብርድ፣ ከአውሬ ወይም ከሌሎች አደጋዎች ይከላከልልናል። የተለያዩ የመጠለያ ዓይነት አሠራሮች አሉ።

- ተማሪዎች! መጠለያ ከምን ከምን ነገሮች ይሠራል?
- በአካባቢያችሁ ያሉ መጠለያዎች ከምን ከምን እንደተሠሩ ለመምህራችሁ ግለጹ።

የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት መጠለያዎቹ ከምን ከምን እንደተሠሩ ለመምህራችሁ ግለጹ።





ሥዕል 2.12 ከተለያዩ ቁሳቁሶች የተሠሩ መጠለያዎች

በአጠቃላይ መጠለያ ከጭቃ፣ ከሣር፣ ከቆርቆሮ፣ ከብረት፣ ከመስታወት፣ ከሲሚንቶ፣ ከሸክላ፣ ከድንጋይ፣ ከእንጨትና ከመሳሰሉት ሊሠራ ይችላል።

## መልመጃ 2.6

ሀ. የሚከተሉትን ሥዕሎች አስተውሳችሁ ተመልከቱ። በመቀጠል በ#ሀ; ረድፍ የሚገኙትን የቤት ዓይነቶች በ#ለ; ረድፍ ላይ ከሚገኙት የቤት መሥሪያ ጥሬ ዕቃዎች ጋር በማስመር አዛምዱ።

#ሀ;






#ለ;

ሀ. ጭቃ፣ ቆርቆሮ፣ ድንጋይ፣ እንጨት

ለ. ሲሚንቶ፣ ብረታ ብረት፣ መስታወት፣ ድንጋይ

ሐ. ሲሚንቶ፣ ሸክላ፣ ቆርቆሮ፣ ድንጋይ

መ. ሣር፣ እንጨት

## 2.3 የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡- |
| • የቤትና የቢሮ ዕቃዎችን ስሞች ትጠቅሳላችሁ፡፡ |
| • የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ምሳሌዎች ትሰጣላችሁ፡፡ |
| • ለቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውሉ እቃዎችን ስሞች ትጠቅሳላችሁ፡፡ |
| • ስለአንዳንድ የቤትና የቢሮ እቃዎች ጥቅሞች ትገልጻላችሁ፡፡ |
| • ስለአንዳንድ የኤሌክትሪክ እቃዎች ጥቅሞች ትገልጻላችሁ፡፡ |
| • የቤት ውስጥ አደጋዎችን ትለያላችሁ፡፡ |
| • የቤት ውስጥ እቃዎችን ለመሥራት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ትጠቅሳላችሁ፡፡ |
| • የቤት ውስጥ እቃዎችን እንዴት እንደምትጠቀሙባቸውና ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባችሁ ትገልጻላችሁ፡፡ |
| • ለቤት ውስጥ እቃዎች የሚደረገውን ጥንቃቄ በተግባር ታሳያላችሁ፡፡ |
| • የቤት ውስጥ አደጋዎችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ትገልጻላችሁ፡፡ |

**ቁልፍ ቃላት**

- የቤት ውስጥ ዕቃዎች
- የቢሮ ዕቃዎች
- የኤሌክትሪክ ዕቃዎች

### 1. የቤት ውስጥ የመገልገያ ቁሳቁሶች

- ተማሪዎች! የቤት ውስጥ የመገልገያ ቁሳቁሶች የሚባሉት እነማን ናቸው?

የቤት ውስጥ የመገልገያ ቁሳቁሶች በሦስት ይመደባሉ::

እነርሱም፡-

ሀ. የቤትና የቢሮ እቃዎች

ለ. የኤሌክትሪክ እቃዎች

ሐ. የመመገቢያና የወጥ ቤት እቃዎች ናቸው፡፡

### ሀ. የቤትና የቢሮ ዕቃዎች

ተማሪዎች! የቤትና የቢሮ ዕቃዎች የሚባሉት ምን ምንድን ናቸው? ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት ለመምህራችሁ ምሳሌዎችን ንገሩ፡፡

ተማሪዎች! ከዚህ በታች የሚገኙትን ሥዕሎች ተመልከቱ::



ከእንጨት የተሠራ አልጋ



የዕቃ ማስቀመጫ ቡፌ



ልብሶችን ለማስቀመጥ የሚያገለግል ቁምሳጥን



የቢሮ ጠረጴዛና ወንበሮች



ሶፋ



ካውያ





ጀበናና ስኒዎች



የመመገቢያ እና የወጥ ቤት ዕቃዎች

ሥዕል 2.13 የተለያዩ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች

ከላይ ከቀረቡት ሥዕሎች ምን ተረዳችሁ?


## ለ. የኤሌክትሪክ ዕቃዎች

**ተማሪዎች!** የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ስንል ምን ማለታችን ነው? ቤታችሁ ውስጥ ያሉ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ምሳሌ ለመምህራችሁ ንገሩ።

**የሚከተሉትን ሥዕሎች በደንብ ተመልከቱ።**



ቴሌቪዥን



ሬዲዮ



ቴፕ



ተንቀሳቃሽ ስልክ



ካውያ



ማቀዝቀዣ



አምፖል



የእንጀራ ምጣድ

**ሥዕል 2.14 የተለያዩ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች**

የኤሌክትሪክ ዕቃዎች የኤሌክትሪክ ኃይልን በመጠቀም የምንገለገልባቸው ዕቃዎች ናቸው። የኤሌክትሪክ እቃዎችን ስንጠቀም ከፍተኛ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባናል። ምክንያቱም ካልተጠነቀቅን ጉዳት ሊደርስብን ይችላል። ስለዚህ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ለመጠቀም ስትፈልጉ ወላጆቻችሁ ወይም ታላላቆቻችሁ እንዲረዷቸው መጠየቅ ይገባችኋል።

- የኤሌክትሪክ ዕቃዎች ስንጠቀም ጉዳት እንዳይደርስብን ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለብን?
- በቤት ውስጥ ሊያጋጥሙን የሚችሉ አደጋዎች ምን ምንድን ናቸው?
- በቤት ውስጥ አደጋ እንዳይገጥመን ምን ማድረግ አለብን?

## ሐ. የወጥ ቤት እና የመመገቢያ እቃዎች

- **ተማሪዎች!** ወጥ ቤት የሚባለው ምን የሚደረግበት ክፍል ነው?
- የወጥ ቤት ዕቃዎች ለምን ለምን አገልግሎት ይውላሉ? የሚከተሉትን ሥዕሎች በጥንቃቄ ተመልከቷቸው። የወጥ ቤት ዕቃዎቹን ስምና ጥቅሞቻቸውን ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት ለመምህራችሁ ግለፁ።



ሥዕል 2.15 የወጥ ቤትና የመመገቢያ ዕቃዎች

## መልመጃ 2.7

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::**

1. በስዕል 2.15 ከምታዩአቸው ቁሳቁሶች ውስጥ ለወጥ ቤት የሚያገለግሉት የትኞቹ ናቸው? ለመመገቢያ የሚያገለግሉትስ?
2. የቤት ውስጥ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን ስም ዘርዝሩ::
3. በቤት ውስጥ አደጋ እንዳይገጥመን ምን ምን ዓይነት የጥንቃቄ እርምጃዎች መውሰድ አለብን?

### 2. የቤት ውስጥ ዕቃዎች ጥቅም

**ተማሪዎች**! ከዚህ በታች የምትመለከቷቸውን የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ጥቅሞች ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ መልሶቹን ለመምህራችሁ ንገሩ::



ዝርግ ሳህን ለምን ይጠቅማል?



በኤሌክትሪክ ምጣድ ምን ይዘጋጃል?





ጉድጓዳ ሳህኖች ለምን አገልግሎት ይውላሉ?



በሹካ ምን ይደረጋል?



በርጩማ ለምን ያገለግላል?



ማንቆርቆሪያ ለምን ይጠቅማል?



በሸክላ ድስት ምን ይዘጋጃል?



በመሶብ ውስጥ ምን ይቀመጣል?



ካውያ ለምን ይጠቅማል?



የጋዝ ምድጃ ለምን ያገለግላል?

ሥዕል 2.16 የቤት ውስጥ ቁሳቁስ ጥቅሞች

## መልመጃ 2.8

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. ኩባያ ውሃ ለመጠጣት ያገለግላል::
2. እንጀራ በመሶብ ይቀመጣል።
3. ማንኪያ ወጥ ይጨለፍበታል::
4. ቡና የሚጠጣው በማንቆርቆሪያ ነው።

### 3. የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ስመሥራት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች

ተማሪዎች! የቤት ውስጥ ዕቃዎች ከምን ከምን እንደሚሠሩ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት ለመምህራችሁ ንገሩ።

ከዚህ በታች የሚገኙትን ሥዕሎች በጥንቃቄ ከተመለከታችሁ በኋላ ከምን ከምን እንደተሠሩ ተወያይታችሁ ስመምህራችሁ ንገሩ።



ጀበና



ብረትድስት



አልጋ



የቡና ሙቀጫ



ሸክላ ሳህን



የሻይ ማፍሊያ

ሥዕል 2.17 ከተለያዩ ነገሮች የተሠሩ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች

## መልመጃ 2.9


**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ**

1. የቡና ጀበና ከምን ይሠራል?
2. አልጋ ከምን ከምን ይሠራል?
3. ምግብ የምንመገብባቸው ሳህኖች ከምን ከምን ሊሠሩ ይችላሉ?

### 4. የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ስንጠቀምና ስናፀዳ ማድረግ የሚገባን ጥንቃቄ

- **ተማሪዎች!** ብርጭቆ ቢወድቅ ምን ይሆናል?
- የሚሰበሩ እቃዎች በምን ዓይነት ሁኔታ መቀመጥ አለባቸው?
- የኤሌክትሪክ ዕቅዎችስ እርጥበት ቢነካቸው ምን ይሆናሉ?
- በቤት ውስጥ በጥንቃቄ ካልተጠቀምንባቸው አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ዕቃዎች ምን ምን ናቸው?
- በቤት ውስጥ አደጋ ሲያጋጥመን ምን ማድረግ አለብን? መልሱን ለመምህራችሁ ንገሩ::

**ተማሪዎች! ከዚህ በታች የቀረቡትን ሥዕሎች በመመልከት የምንገለገልባቸው ዕቃዎች እንዴት አደጋ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ግለጹ።**




ቢላዋ በአግባቡ ካልተያዘ ምን ጉዳት ያመጣል?



በሥዕሉ የሚታየው ሶኬት ምን ዓይነት አደጋ ያስከትላል?



የጋዝ ምድጃ በጥንቃቄ ባይያዝ ምን አደጋ ያስከትላል?



የጋለ ካውያ መንካት ምን ጉዳት አለው?

**ሥዕል 2.18 አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ የቤት ዕቃዎች**

**ተማሪዎች!** የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ስትጠቀሙና ስታጸዱ ምን ምን ዓይነት ጥንቃቄዎች ማድረግ እንዳለባችሁ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ መልሶቹን ለመምህራችሁ ንገሩ።

**ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ሥዕሎች የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ስንጠቀምና ስናጸዳ ማድረግ የሚገባንን ጥንቃቄ ያሳያሉ።**






የማጠቢያ ቁሳቁሶችን ሕጻናት የማይደርሱበት ቦታ ማስቀመጥ



ዕቃዎችን ስናጸዳ ተሰብረው እንዳይጉዱን በጥንቃቄ ማስቀመጥ



የተመገንባቸውን ዕቃዎች ማጽዳት



ተቀጣጣይ ነገሮች አደጋ እንዳያደርሱ ጥንቃቄ ማድረግ



የቤት ዕቃዎችን በጥንቃቄ ማጽዳት

ሥዕል 2.19 የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን በንጽህና እና በጥንቃቄ መያዝ

ሁሉም የቤት ውስጥ እቃዎች እንዳይሰበሩና እንዳይበላሹ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። የወጥ ቤት እቃዎችን በንጽሕና በመደርደሪያ ውስጥ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። የኤሌክትሪክ እቃዎችን ደግሞ ከእርጥበትና ከአቧራ መጠበቅ ያስፈልጋል። ሌሎች የቤት ውስጥ ዕቃዎችንም በንጽሕና እና በጥንቃቄ መጠቀም አለብን።

በሰውነታችን ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ስለት ያላቸውን ነገሮች በጥንቃቄ መያዝ ይገባናል። ተቀጣጣይ የሆኑና የእሳት አደጋ የሚያስከትሉ ነገሮች ጉዳት እንዳያደርሱብን በአግባቡ መጠቀም እንዲሁም አደጋ ከተከሠተ በፍጥነት ከአካባቢው መራቅ ይጠበቅብናል።

# ማጠቃለያ

- ቤተሰብ አባት፣ እናት እና ልጆችን በአባልነት ይይዛል። በቤታችን ውስጥ አብሮ የሚኖር ዘመድ የቤተሰብ አባል ነው። በቤተሰብ ውስጥ መተሳሰብ፣ መፈቃቀር፣ መከባበር፣ መግባባት፣ መረዳዳት እና ታማኝነት የመሳሰሉት መልካም ግንኙነቶች መገለጫዎች ናቸው።
- ሁሉም የቤተሰብ አባላት የራሳቸው የሥራ ድርሻ እና ኃላፊነት አላቸው:: ወላጆች ለቤተሰቦቻቸው የገቢ ምንጭ በማስገኘት ቤተሰቦቻቸውን ያስተዳድራሉ፤ ልጆቻቸውንም ያዝናናሉ፤ በትምህርትም ይረዷቸዋል።
- ወላጆች ከቤት ውጭ ሥራ በተጨማሪ ቤቶቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በልዩ ልዩ ሁኔታ ይንከባከባሉ። ልጆች ደግሞ ትምህርታቸውን በአግባቡ ይማራሉ፤ ያጠናሉ፤ ታላላቆቻቸውን ያከብራሉ፤ በአቅማቸውም ወላጆቻቸውን ይረዳሉ።
- ለቤተሰባችን ምግብ፣ መጠለያ እና ልብስ ያስፈልጋል። ምግብ ከተለያዩ የግብርና ውጤቶች ይገኛል። መጠለያ ደግሞ እንደ እንጨት ድንጋይ፣ ሲሚንቶ፣ ሸክላ፣ ጭቃና ከመሳሰሉት ነገሮች ሊሠራ ይችላል። ልብሶች ከጥጥ፣ ከበግ ፀጉር /ሱፍ/፣ ከሐር፣ ከቆዳ እና ከመሳሰሉ ነገሮች ሊሠሩ ይችላሉ።
- የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች የተለያዩ ናቸው። እነርሱም የቤትና የቢሮ እቃዎች፣ የኤሌክትሪክ እቃዎች እና የወጥ ቤት እቃዎች ናቸው።
- የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች ጠቃሚ አገልግሎት ስለሚሰጡን በጥንቃቄ መያዝ አለባቸው።
- የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች ጉዳት እንዳያደርሱብን በአግባቡ መጠቀም አለብን።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. እናት አባት እና ልጆች የቤተሰብ አባላት ናቸው።
2. ልጆች ቤተሰባቸውን በአቅማቸው መርዳት ይገባቸዋል።
3. ነጠላ እና ጋቢ ከበግ ፀጉር ይሰራሉ።
4. መጠለያ ሰዎችን ከአውሬ ይከላከላል።
5. ካውያ የወጥ ቤት ዕቃ ነው።

**ለ. በ"ሀ" ሥር የተቀመጡትን በ"ለ" ሥር ካሉት ጋር በመስመር በማገናኘት አዛምዱ።**

| #ሀ; | #ለ; |
|---|---|
| 1. ጋቢ | ሀ. ከቆዳ የሚሠራ |
| 2. ብርድ ልብስ | ለ. ከጥጥ የሚሠራ |
| 3. ቀበቶ | ሐ. ከሐር የሚሠራ |
| 4. የራት ቀሚስ | መ. ከበግ ፀጉር /ሱፍ/ የሚሠራ |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::**

1. በቤተሰብ ውስጥ የልጆች ኃላፊነት ምንድንነው?

   ሀ. ጥናት ማጥናት — ሐ. ቤት ማጽዳት

   ለ. አትክልትን መኮትኮት — መ. ሁሉም መልስ ናቸው

2. ከአተር የሚዘጋጅ የምግብ ዓይነት ምንድን ነው?

   ሀ. ፓስታ ለ. ጭማቂ ሐ. ሽሮ ወጥ መ. ዳቦ

3. ጎጆ ቤት ከምን ይሠራል?

   ሀ. ከሳር — ሐ. ከጭቃ

   ለ. ከእንጨት — መ. ሁሉም መልስ ናቸው

4.በቅዝቃዜ ጊዜ የሚለበሰው የልብስ ዓይነት የትኛው ነው?

   ሀ. ሹራብ ለ. ካናቴራ ሐ. ነጠላ መ. ሸሚዝ

5. የኤሌክትሪክ ዕቃ ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ቴሌቪዥን — ሐ. ማቀዝቀዣ

   ለ. የጋዝ ምድጃ — መ. መልሱ የለም

## ፍተሻ

*ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሳጥኖች ውስጥ በማስቀመጥ አመልክቱ::*

1. የቤተሰቦቼን አባላት በመዘርዘር የሥራ መስኮቻቸውን እናገራለሁ::
2. የምንመገባቸው ምግቦች የግብርና (የእርሻ) ውጤቶች መሆናቸውንና ምንጮቻቸውን እጠቅሳለሁ::
3. በቤቴ የሚገኙ ተክሎችና የተክሎች ውጤቶችን መጥራት እችላለሁ::
4. ተክሎችን እንከባከባለሁ::
5. ልብሶችና መጠለያዎች ከምን እንደተሠሩ መግለጽ እችላለሁ::
6. የተለያዩ ልብሶችንና መጠለያ ዓይነቶችን እለያለሁ::
7. አንዳንድ የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ስሞች መጥቀስ እችላለሁ::
8. የቤት ውስጥ ዕቃዎችን ጥቅምና ከምን እንደተሰሩ መናገር እችላለሁ::
9. የቤት ውስጥ ዕቃዎችን በጥንቃቄ እይዛለሁ::

# ምዕራፍ ሦስት

# ትምህርት ቤታችን

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የትምህርት ቤታችሁን ግቢ በማጥናት በውስጡ ስለሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ታስረዳላችሁ፡፡
- በትምህርት ቤት፣ በቤትና በጐረቤት ለሚገኙ ሕጐችና ደንቦች ያላችሁን አክብሮት በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- በትምህርት ቤት በቤትና በጐረቤት ሊኖር የሚገባውን ጤናማ የእርስ በእርስ ግንኙነቶችን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- የታወቁ የመንገድ ላይ አደጋዎችን በመዘርዘር መከላከያ ዘዴዎችን ታስረዳላችሁ፡፡
- ወረቀት በመጠቀም ዎላንደና የነፋስ ቱርቢና ትሠራላችሁ፡፡
- ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎቶችን ማለትም፡- መመልከትን፣ መጠየቅን፣ መግባባትን፣ መሳይ ቅርጻቅርጾች መሥራትንና ተባብሮ መሥራትን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡

## 3.1 የትምህርት ቤታችን ግቢ

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦<br>• የትምህርት ቤታችሁን ግቢ ሁኔታ ትገልጻላችሁ::<br>• በትምህርት ቤታችሁ ስላሉት እንቅስቃሴዎች ትገልጻላችሁ።<br>• በትምህርት ቤታችሁ እንዴት መፀዳጃ ቤቶችን መጠቀም እንዳለባችሁ ትገልጻላችሁ።<br>• ከማን ጋር እንደምትጫወቱ ትገልጻላችሁ።<br>• እንዴት ንጹኛ እንደምታፈሩ ታስረዳላችሁ። |

**ቁልፍ ቃላት**

- የትምህርት ቤት ግቢ
- የትምህርት ቤት ውስጥ እንቅስቃሴዎች

### 3.1.1 የትምህርት ቤት ግቢ አቀማመጥና ደዞታው

- ተማሪዎች! ትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ምን ምን ነገሮች ይገኛሉ? ምድረ ግቢው ያማረና ለመማሪያነት ምቹ ነው?
- በትምህርት ቤታችሁ ግቢ ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች በሥዕል ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

**መልመጃ 3.1**

ተማሪዎች! ከዚህ በታች የሚገኘውን ሥዕል በደንብ ተመልከቱ። ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት በሥዕሉ የምታዩአቸውን ነገሮች ለመምህራችሁ ንገሩ።




1. ሥዕሉ የምን ሥዕል ነው?
2. በሥዕሉ ውስጥ ምን ምን ነገሮች ይታያሉ?
3. ትምህርት ቤታችሁ መጻዳጃ ቤትና ውሃ አለው? መጫወቻ ሜዳስ?

## መልመጃ 3.2

ከላይ የቀረበውን ሥዕል በመመልከት ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. ትምህርት ቤቱ የመጫወቻ ሜዳ አለው።
2. ሰንደቅ ዓላማው ከትምህርት ቤቱ በስተጀላ ተሰቅሎ ይታያል።
3. ትምህርት ቤቱ የመጻዳጃ ቤት የለውም።

**ተማሪዎች!** ከሥዕሉ እንደምትመለከቱት በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ:-

- መማሪያ ክፍሎች
- ቢሮዎች
- መጻዳጃ ቤቶች
- የመጫወቻ ሜዳ
- ዛፎች

- አበቦች
- ቤተመጻሕፍትና የመሳሰሉት ይገኛሉ።

**ተማሪዎች!**

1. የትምህርት ቤታችሁ መጸዳጃ ቤቶች ንጽሕናቸው የተጠበቀ ነው?
2. እናንተስ በመጸዳጃ ቤቶቹ በአግባቡ ትጠቀማላችሁ?
3. መጸዳጃ ቤት ተጠቅማችሁ ስትወጡ እጆቻችሁን ትታጠባላችሁ? ከላይ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት ለመምህራችሁ ንገሩ።

**እስቲ ከዚህ በታች ያለውን ሥዕል ተመልከቱ።**




በሥዕሉ የምትታየው ልጅ ምን እያደረገች ነው?

**ተማሪዎች!** በትምህርት ቤት ቆይታችሁ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለባችሁ።

- መጸዳጃ ቤቶችን ሳታቆሽሹ በአግባቡ መጠቀም
- ከመጸዳጃ ቤት መልስ እጃችሁን መታጠብ
- አትክልቶችን መንከባከብ
- ቆሻሻ በየቦታው አለመጣል
- የትምህርት ቤትን ንብረት መንከባከብና መጠበቅ

## መልመጃ 3.3

**የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. ከመጸዳጃ ቤት መልስ እጃችንን መታጠብ አለብን::
2. የትምህርት ቤትን ግቢ ማቆሸሽ ተገቢ አይደለም::


### 3.1.2 በትምህርት ቤት ውስጥ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች

1. በትምህርት ቤታችሁ ምን ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎች ይካሄዳሉ?
2. በትምህርት ቤታችሁ የሚገኙ ክበባትን ስም ዘርዝሩ::
3. እናንተ በየትኞቹ ክበባት ትሳተፋላችሁ?

**በትምህርት ቤታችሁ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችን በደብተራችሁ ላይ በዝርዝር በመጻፍ ስመምህራችሁ አሳዩ:: ቀጥሎ ያለውን ሥዕል ደግሞ በደንብ ተመልከቱ::**



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ሕጻናቱ ምን እያደረጉ ነው?



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?
- ልጆቹ የሚሠሩት ሥራ ለምን ይጠቅማል?

**ሥዕል 3.1 በትምህርት ቤት ውስጥ የሚካሄዱ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች**

በሥዕል 3.1 ላይ ምን ምን ተመለከታችሁ?

ተማሪዎች በሥነሥርዓት እጃቸውን ሲታጠቡ፣ የትምህርት ቤቱን ግቢ ሲንከባከቡ፣ የእግር ኳስ ሲጫወቱ ተመለከታችሁ?

**በአጠቃላይ በትምህርት ቤት ውስጥ ከሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ውስጥ፦**

- በጎብረት መጫወት
- በልዩ ልዩ ክበባት መሳተፍ
- በስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ
- ምድረ ግቢን መንከባከብ
- ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መከባበርና መተባበር ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## መልመጃ 3.4

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. ተማሪዎች በጎብረት መጫወታቸው ምን ጥቅም አለው?
2. በትምህርት ቤታችሁ የምን የምን ክበባት አሉ?
3. በትምህርት ቤታችሁ የሚካሄዱትን የስፖርታዊ እንቅስቃሴ ዓይነቶች ዘርዝሩ።

## 3.2 ደንቦችንና ሥነ-ሥርዓትን ማክበር

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦<br>• ለትምህርት ቤት ደንቦችና ሥነ ሥርዓቶች ያላችሁን አክብሮት በተግባር ታሳያላችሁ፡፡ |

**ቁልፍ ቃል**

- የትምህርት ቤት ሕጐችና ደንቦች

### 3.2.1 የትምህርት ቤት ደንቦችና ሥነ-ሥርዓቶች

**ተማሪዎች! የትምህርት ቤታችሁን ደንቦችና ሥነ-ሥርዓቶች ታውቃላችሁ?**

**በትምህርት ቤት ውስጥ ሊኖሩ የሚገቡ ደንቦችና ሥነ-ሥርዓቶችን በቡድን በቡድን ሆናችሁ አዘጋጁ፡፡**

የትምህርት ቤት ደንቦችና ሥነ-ሥርዓቶች የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ::

- የትምህርት መሣሪያዎችን አሟልቶ በአግባቡ መያዝ
- የትምህርት ሰዓትን አክብሮ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት
- የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ መልበስ
- ትምህርትን በአግባቡ መከታተል
- በክፍልም ሆነ በቅጥር ግቢ ውስጥ አለመረበሽ
- የክፍልና የቤት ሥራዎችን በወቅቱ መሥራት
- የትምህርት ቤትን ንብረት መጠበቅና መንከባከብ
- ከሌሎች ተማሪዎች ጋር አለመጣላት፣ አለመደባደብ
- መምህራንንና የአስተዳደር ሠራተኞችን ማክበር

### 3.2.2 ማኅበራዊ እሴቶች በቤትና በጐረቤት

**ተማሪዎች! በቤትና በጐረቤት ሊኖለብቱ የሚገቡት ምን ምን ማኅበራዊ እሴቶች ናቸው? በዝርዝር ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

## ከዚህ በታች የሚገኙትን ሥዕሎች ተመልከቱ።



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ልጁ ምን እያደረገ ነው?



ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?

### ሥዕል 3.2 የትምህርት ቤት ደንቦችና ሥነ-ሥርዓቶች ሲከበሩ



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ልጁ ምን እያደረገ ነው?



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ምን እየሠሩ ነው?



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ልጆቹ ምን እያደረጉ ናቸው?

ሥዕል 3.3 ማኅበራዊ እሴቶች በተግባር ሲገለጹ

**ተማሪዎች!** የሚከተሉትን ማኅበራዊ እሴቶች በቤትና በጐረቤት ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸኋል፡፡

- ወላጆችንና ታላላቆችን ማክበር
- ለወላጆች መታዘዝ
- ለጐረቤቶቻችሁ አክብሮት መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

## መልመጃ 3.5

የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

1. የጐረቤት ልጆች መረዳዳት የለባቸውም፡፡
2. ልጆች ለቤተሰብ መታዘዝ አለባቸው፡፡
3. ቤተሰባችንን ማክበር ፍቅርን ይጨምራል፡፡

## 3.3 መልካም የእርስ በእርስ ግንኙነት

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-<br>• በቤትና በጐረቤት መኖር ለሚገባው መልካም ግንኙነት ተገገር ለመሆን ፈቃደኝነታችሁን ትገልጻላችሁ፡፡<br>• በትምህርት ቤት መኖር የሚገባውን መልካም ግንኙነት በተግባር ታሳያላችሁ፡፡ |

## 3.3.1 በትምህርት ቤት፣ በመኖሪያ ቤትና በጐረቤት ሊኖር የሚገባው ግንኙነት

**ተማሪዎች!** በትምህርት ቤት፣ በመኖሪያ ቤትና በጐረቤት ሊኖር የሚገባው ግንኙነት ምን መምሰል አለበት? በቡድን ሆናችሁ በመወያየት የደረሳችሁበትን ለመምህራችሁ ግለጹ።

**ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች ተመልከቱ።**



ሀ. ልጆቹ ምን እየሠሩ ነው?
የሚሠሩት ሥራ ለምን ይጠቅማል?



ለ. ልጆች የታመመች ጓደኛቸውን ሲጠይቁ



ሐ. ልጆች በጋራ አካባቢያቸውን ሲያለሙ

**ሥዕል 3.4 መልካም የእርስ በእርስ ግንኙነት**

*ተማሪዎች! ከሥዕሎቹ ምን ተረዳችሁ?*

ሰላምታ መለዋወጥ፣ መግባባት፣ መተባበር፣ ፍቅርን ማሳየት፣ ሰዎችን መርዳት የመልካም ግንኙነት መገለጫዎች ናቸው።

## መልመጃ 3.6

**ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ::**

1. ጎረቤታሞች ተባብረው መንደራቸውን ማጽዳት ይኖርባቸዋል::
2. ሰላምታ መስጠት የመከባበር መገለጫ ነው::
3. በሠርግ ሥነ-ሥርዓት ወቅት ጎረቤታሞች ደስታቸውን አብረው ይካፈላሉ::
4. በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች እድር አያስፈልጋቸውም::

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ::**

1. ከሚከተሉት ውስጥ መልካም የጉርብትና ሥነ ምግባር የቱ ነው?

   ሀ. አካባቢን ማቆሸሽ ሐ. የታመመን መጠየቅ

   ለ. ጎረቤትን በጩኸት መረበሽ መ. ሰላምታ አለመስጠት

2. በትምህርት ቤት ጥሩ ሥነ ምግባር ያልሆነው የትኛው ነው?


   ሀ. መከባበር ሐ. መደባደብ

   ለ. አብሮ መጫወት መ. መልሱ የለም

## 3.4 የመንገድ ደኅንነት

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ:- <br>• የመኪና መንገድ አደጋዎችን አስከፊ ጉዳት ትገልጻላችሁ::<br>• የመኪና መንገድ አደጋዎችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ትገልጻላችሁ::<br>• የመንገድ ማቋረጥ ደንቦችን በማወቅ ሌሎችን መርዳት ትለማመዳላችሁ:: |

ከዚህ በታች የቀረቡትን ሥዕሎች በጥንቃቄ ተመልከቱ።



- ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?
- በእግረኛ ማቋረጫ ላይ መሻገር ለምን ይጠቅማል?



- ሕጻናቱ ምን እያደረጉ ነው?
- እያደረጉት ያለው ተግባር ምን ጉዳት ያስከትላል?


ሥዕል 3.5 የመኪና መንገድ አጠቃቀም

## 3.4.1 የመንገድ ላይ አደጋዎች

ተማሪዎች! በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ።

1. የመንገድ ላይ አደጋ መንሥኤዎች ምን ምንድን ናቸው?
2. የመንገድ ላይ አደጋ የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው?
3. የመንገድ ላይ አደጋን ለማስወገድ ምን መደረግ አለበት?

የሚከተሉትን ሥዕሎች ተመልከቱ



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?
- በሥዕሉ ላይ እንደሚታየው በዚህ ሁኔታ መንገድ ማቋረጣቸው ትክክል ነው?



- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- አደጋው ለምን ተፈጠረ?



- ሕጻናቱ ምን እያደረጉ ነው?
- ይህ ሁኔታ ምን ያስከትላል?



የጐርፍ መሳት አደጋ

ሥዕል 3.6 የመንገድ ላይ አደጋዎች

ዋና ዋናዎቹ የመንገድ ላይ አደጋ መንሥኤዎች፡-


1. ግራና ቀኝ ሳያዩ የመኪና መንገድ ማቋረጥ
2. የአሽከርካሪዎች በግዴለሽነት ማሽከርከር (ለእግረኛ ቅድሚያ ያለመስጠት)
3. በውሾችና በሌሎች እንስሳት መደናገጥ
4. የጐርፍ ውኃ መሳት
5. መኪና መንገድ ላይ ኳስ መጫወትና የመሳሰሉት ናቸው።

**ተማሪዎች!** የመንገድ ላይ አደጋ መንሥኤዎች ምን ምን እንደሆኑ ቀደም ሲል ተረድታችኋል። እነዚህን አደጋዎች እንዴት መከላከል ይቻላል? በቡድን ተወያይታችሁ መልሶቹን ለመምህራችሁ ንገሩ።

በመንገድ ላይ የሚከሰቱ የተለያዩ አደጋዎችን ለመከላከል የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ ይገባችኋል፡፡

- በመኪና መንገድ ዳር ስትጓዙ ጠንቃቃና ንቁ መሆን
- አደገኛ በሆነ ሁኔታ መንገድ አለማቋረጥ
- ድልድዮችና አንሸራታች ቁልቁለቶች ላይ ስትጓዙ በጥንቃቄ ማለፍ
- በመንገድ ላይ ከመጫወት መቆጠብ
- የትራፊክ ሕጐችን ተግባራዊ እያደረጉ መጓዝ
- የእግረኛ ማቋረጫ መስመሮችን መጠቀም
- የመኪና መንገድ ስታቋርጡ አረንጓዴ መብራት መብራቱን ማረጋገጥ

**የሚከተሉትን ሥዕሎች በደንብ ተመልከቱ፡፡**



ሀ. ትክክለኛ የመኪና መንገድ ማቋረጫ



ለ. ተገቢ ባልሆነ ቦታ መንገድ ማቋረጥ



ሀ. ተገቢ ያልሆነ የኳስ መጫወቻ ስፍራ



ለ. ተገቢ የሆነ የኳስ መጫወቻ ቦታ

ሥዕል 3.7 የተለያዩ የልጆች እንቅስቃሴዎች

## መልመጃ 3.7

**የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ::**

1. በመኪና መንገድ ላይ ሲያቋርጡ ጠንቃቃና ንቁ መሆን ያስፈልጋል::
2. አደገኛ በሆነ መንገድ ማቋረጥ የለብንም::
3. የትራፊክ ሕጐች ባይታወቁም ችግር የለውም::
4. የጐዳና ውሾች ለአደጋ ያጋልጣሉ::
5. በመኪና መንገድ ሲጓዙ ግራና ቀኝ አይቶ መሻገር ተገቢ ነው::
6. በበረገጉ እንስሳት አደጋ ሊደርስ ይችላል::

## 3.5 በትምህርት ቤታችን ስማከናወን የምንችሳቸው እንቅስቃሴዎች

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡- <br> • በወረቀት ምላንዶና በነፋስ የሚሽከረከር ፉራፉሬ ትሠራላችሁ:: |


### 3.5.1 ወረቀት በመጠቀም መሳይ ቅርፃችን መሥራት

**ተማሪዎች!** ከወረቀት ምን ምን መጫወቻዎችን መሥራት ይቻላል?

ወላንዶና የነፋስ ቱርቢና እንዴት ይሠራሉ?

በሥዕሉ ላይ የምታዩአቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ለመምህራችሁ ንገሩ::





- ይህ የምን ሥዕል ነው?
- የተሠራው ከምንድን ነው?
- ልጆቹ ምን እያደረጉ ነው?

ሥዕል 3.8 ከወረቀት የተሠሩ የተለያዩ መጫወቻዎች

## መልመጃ 3.8

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. ወላንዶ ከምን ይሠራል?
2. ሌሎች ከወረቀት የሚሠሩ መጫወቻዎችን ጥቀሱ::

# ማጠቃለያ

- በትምህርት ቤታችን ውስጥ የተለያዩ ነገሮች ይገኛሉ። ለምሳሌ የመማሪያ ክፍሎች፣ የመምህራን ክፍል፣ የርዕሰ መምህራን ክፍል፣ ሰንደቅ ዓላማ፣ የመጫወቻ ሜዳ፣ መጸዳጃ ክፍሎች እና የውሃ መጠጫ ቦታ ይገኛሉ።
- ትምህርት ቤታችን የተለያዩ ደንቦችና የሥነሥርዓት መመሪያዎች አሉት። ደንቦቹንም ሆነ ሥነ ሥርዓቶቹን ማክበር ተገቢ ነው። ከእነዚህም መካከል፦
  - የትምህርት መሣሪያዎችን አሟልቶ መምጣት
  - የትምህርት ሰዓትን ማክበር
  - ትምህርት በአግባቡ መከታተል
  - የደንብ ልብስን በሥርዓቱ መልበስ
  - የክፍልና የቤት ሥራዎችን በወቅቱ መሥራት
  - የትምህርት ቤቱን ንብረት በአግባቡ መያዝ
  - ለመምህራንና ለሌሎች የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች መታዘዝና አክብሮት ማሳየት
  - ከሌሎች ተማሪዎች ጋር አለመጣላትና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።
- በቤትና በጐረቤት አካባቢ የተለያዩ ማኅበራዊ እሴቶች አሉ። ለምሳሌ አክብሮት መስጠት፣ መታዘዝ፣ መረዳዳት፣ መዋደድና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።
- የመንገድ ደኅንነት ሕጐችና ደንቦችም በጣም አስፈላጊ ናቸው። ምክንያቱም ሕጐችና ደንቦችን ማክበር ራሳችንን ከመንገድ ላይ አደጋዎች እንድንጠብቅ ይረዳናል።
- በትምህርት ቤታችን ውስጥ ልናከናውናቸው የምንችላቸው እንቅስቃሴዎችና ልምዶች አሉ። ተማሪዎች እናንተም ወረቀት፣ እንጨትና ክር በመጠቀም ወላንዶ ወይም የነፋስ ቱርቢና (ፉራፍሬ) መሥራት ትችላላችሁ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. በትምህርት ቤት ውስጥ የኳስ መጫወቻ ሜዳ መኖር አለበት።
2. የትምህርት ሰዓትን ማክበር ከትምህርት ቤት ደንቦች ውስጥ አንዱ ነው።
3. ለጐረቤቶቻችን አክብሮት መስጠት አያስፈልግም።
4. ግራና ቀኝ ሳያዩ መንገድ ማቋረጥ አደጋ ያስከትላል።
5. ወላንዶ ከቆርቆሮ ይሠራል።

**ለ. በ"ሀ" ሥር የተቀመጡትን በ"ለ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ።**

| #ሀ; | #ለ; |
|---|---|
| 1. ሰንደቅ ዓላማ | ሀ. ጥሩ የርስ በርስ ግንኙነት |
| 2. መማሪያ ክፍሎች | ለ. ከወረቀት የሚሰራ መጫወቻ |
| 3. አክብሮት መስጠት | ሐ. የትምህርት ቤት ደንብ |
| 4. የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ መልበስ | መ. የሀገር መለያ ዓርማ |
| 5. ወላንዶ | ሠ. ትምህርት የምንማርበት ክፍል |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።**

1. ከሚከተሉት ውስጥ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኘው የቱ ነው?
   ሀ. መማሪያ ክፍል ሐ. መጸዳጃ ቤት
   ለ. ሰንደቅ ዓላማ መ. ሁሉም መልስ ናቸው
2. በትምህርት ቤት ውስጥ በጥቁር ሰሌዳ ላይ የሚጻፈው በምንድን ነው?
   ሀ. እርሳስ ለ. ጠመኔ ሐ. እስክሪፕቶ መ. ፓርከር
3. የትምህርት ቤት ደንብ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ሰዓት ማክበር ሐ. መንገድ ግራና ቀኝ አይቶ ማቋረጥ
   ለ. የደንብ ልብስ መ. የቤት ሥራና የክፍል ሥራ መሥራት
4. የመንገድ ላይ አደጋ ሊከሰት የሚችለው፡-
   ሀ. ግራ ቀኝ ሳያዩ በማቋረጥ ሐ. በእንስሳት መበርገግ
   ለ. በግዴለሽነት በማሽከርከር መ. ሁሉም መልስ ናቸው
5. ከወረቀት የሚሠራ መጫወቻ ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. መዝለያ ገመድ
   ለ. ወላንዶ
   ሐ. የንፋስ ቱርቢና (ፉራፍሬ)

## ፍተሻ

*ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሳጥኖች ውስጥ በማስቀመጥ አመልክቱ::*

1. በትምህርት ቤቴ ግቢ ውስጥ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችን አስረዳለሁ::
2. በትምህርት ቤት፣ በቤትና በጐረቤት ለሚገኙ ሕጎችና ደንቦች ያለኝን አክብሮት በተግባር አሳያለሁ::
3. በትምህርት ቤት፣ በቤትና በጎረቤት ሊኖር የሚገባውን ጤናማ የእርስ በእርስ ግንኙነት በተግባር አሳያለሁ::
4. የታወቁ የመንገድ ላይ አደጋዎችን በመዘርዘር መከላከያ ዘዴዎችን አስረዳለሁ::
5. ወረቀት በመጠቀም ወላንዶና የንፋስ ቱርቢና እሠራለሁ::
6. ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎቶችን ማለትም መመልከትን ፣ መጠየቅን፣ መግባባትን፣ መሳይ ቅርፃ ቅርፆች መስራትንና ተባብሮ መሥራትን በተግባር አሳያለሁ::

# ምዕራፍ አራት

## መረዳችን

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-**

- የትምህርት ቤቶቻችሁን፣ የመኖሪያ ቤቶቻችሁንና የወረዳችሁን አንጻራዊ መገኛ ታመለክታላችሁ::
- የአየር፣ የውሃና የአፈር ባህርያትን ትገልጻላችሁ፣ ጥቅማቸውንም ትናገራላችሁ::
- አፈር (ጭቃ) በመጠቀም የተለያዩ መሳይ ቅርጾችንና ምስሎችን ትሰራላችሁ::
- ተክሎችን በመጠናቸውና በዓይነታቸው በመመደብ ጥቅማቸውን ትናገራላችሁ፣ ሊደረግላቸው የሚገባውን እንክብካቤም በተግባር ታሳያላችሁ::
- እንስሳትን የቤትና የዱር እንስሳት ብላችሁ በመመደብ ጥቅማቸውን ትናገራላችሁ:: ሊደረግላቸው የሚገባውን እንክብካቤም በተግባር ታሳያላችሁ::
- የተለያዩ የሥራ ዓይነቶችን የግልና የመንግሥት ብላችሁ በመመደብ የሥራን ጥቅም ትናገራላችሁ፣ በዕድሜያችሁ ደረጃ ለሥራ ያላችሁን ክብርና ፍቅር በተግባር ታሳያላችሁ::
- የመጓጓዣን ጥቅም በመናገር የባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎች ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ::
- ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎቶችን ማለትም:- መመልከትን፣ መጠየቅን፣ መግባባትን፣ ተባብሮ መሥራትንና መመደብን በተግባር ታሳያላችሁ::

## 4.1 የወረዳችን መገኛ

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡-<br>• አቅጣጫዎችን ግራና ቀኝ፣ ፊትና ኋላ በማለት ትለያላችሁ፡፡<br>• የትምህርት ቤቶቻችሁን፣ የመኖሪያ ቤቶቻችሁንና የጐረቤቶቻችሁን አካባቢያዊ መገኛ ታመለክታላችሁ፡፡ |

**ቁልፍ ቃላት**

- አቅጣጫ
- መገኛ

### 4.1.1 አቅጣጫዎችን መናገር

ተማሪዎች! አቅጣጫ ምንድን ነው? እንዴት ይገለጻል? ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡


አቅጣጫ አንድ ቦታ ወይም አንድ ነገር በአካባቢው ካሉት ቋሚ ነገሮች ለምሳሌ ሕንፃዎች፣ ተራራዎች፣ ወንዞች፣ መንገዶችና ሌሎች ነገሮች አንጻር የሚገኝበት ሥፍራ አመላካች ነው፡፡

የአንድ ቦታ ወይም ነገር አቅጣጫ ለመግለጽ፡-

- ግራና ቀኝ
- አጠገብ
- ፊት ለፊት
- ጀርባ
- ጐን
- ፊትና ኋላ የሚሉትን አቅጣጫ አመላካች ስያሜዎችና ቅጽሎች መጠቀም ይቻላል፡፡

## ከዚህ በታች የሚገኙትን ሥዕሎች አስተውላችሁ ተመልከቱ

ሀ. በሥዕሉ የሚታዩት ሰው ከዛፉ በየትኛው አቅጣጫ ቆመዋል?



ዛፉ ከሰውየው በስተቀኝ በኩል ወይም አጠገብ ይገኛል

ለ. በሥዕሉ የሚታየው ኳስ ከልጁ በየት በኩል ይገኛል?



ኳሱ በልጁ ግራ እግር አጠገብ ይገኛል

ሐ. በሥዕሉ የሚታየው ሰንደቅ ዓላማ የት ይገኛል?




ሰንደቅ ዓላማው ከመማሪያ ክፍሎች ፊት ለፊት ተሰቅሏል

መ. በሥዕሉ ከሚታየው ቤት ጀርባ የሚታየው ምንድን ነው?

ሠ. በሥዕሉ የሚታዩትን ልጆች መገኛ ተናገሩ።



ከቤቱ ጀርባ ትላልቅ ዛፎች ይታያሉ




ዐቢይ ከሃና ፊት ቆሟል ሐና ደግሞ ከዐቢይ ኋላ ቆማለች

ረ. በሥዕሉ ከሚታየው ልጅ በስተቀኝ በኩል የሚገኘው ምንድን ነው? በስተግራ በኩል ያለውስ ምንድን ነው?



ከልጁ በስተግራ የመኖሪያ ቤት፣ በስተቀኝ በኩል ደግሞ ዛፍ ይገኛል።

ሥዕል 4.1 አንጻራዊ መገኛ

## መልመጃ 4.1

**ሀ. የሚከተለውን ሥዕል በመመልከት የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።**




1. ቤተ መጻሕፍቱ የት ይገኛል?
2. የጥበቃ ሠራተኞች ቤት መገኛ የት ነው?
3. የመምህራን ማረፊያ ክፍል የሚገኘው የት ነው?
4. የሰንደቅ ዓላማው መገኛ የት ነው?
5. ከኪስ መጫወቻ ሜዳው በስተግራ የሚገኘው ምንድን ነው?
6. የኪስ መጫወቻውን ሜዳ መገኛ ከሰንደቅ ዓላማው፣ ከመማሪያ ክፍሎችና ከቤተ መጻሕፍቱ አንጻር ግለጹ።

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከትምህርት ቤታችሁ አንጻር መልሱ።**

1. የመማሪያ ክፍላችሁ የት ይገኛል?
2. የሦስተኛ "ሀ" ተማሪዎች የሚማሩበት ክፍል የሚገኘው የት ነው?
3. የተማሪዎች የመጸዳጃ ቤት የት ይገኛል?
4. የውኃ ቧንቧው የሚገኘው የት ነው?
5. ቤተ መጻሕፍቱ የት ይገኛል?
6. የኪስ መጫወቻ ሥፍራው የት ነው?

## 4.2 በዙሪያችን የሚገኙ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦<br>• የአየርን መኖር በተግባር ታሳያላችሁ።<br>• አየር ለምን እንደሚያስፈልግ ትገልጻላችሁ።<br>• ውኃ በኩሬ፣ በጉድጓድ፣ በምንጮችና በወንዞች እንደሚገኝ ታስረዳላችሁ።<br>• የውኃን ጠቀሜታ ትናገራላችሁ።<br>• አፈር ለተክሎች የሚሰጠውን ጥቅም ትናገራላችሁ።<br>• በሸክላ አፈር ቀላል መሳይ ቅርጾችንና ምሥሎችን ትሠራላችሁ። |

**ቁልፍ ቃላት**


- አየር
- አፈር
- ውኃ

### 4.2.1 አየር

#### ሀ. አየር ስለመኖሩ

ተማሪዎች! አየር መኖሩን እንዴት እናውቃለን? የአየር መኖርን ለማስረዳት የሚችሉ ምሳሌዎችን መስጠት ትችላላችሁ? ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሶቹን ለመምህራችሁ ንገሩ።

ቀጥሎ ያሉትን ሥዕሎች በጥንቃቄ ተመልከቱ።



የፊኛ በአየር መሞላት

ሀ. በሥዕሉ የሚታየው ልጅ ምን እያደረገ ነው?



የውሃ ፍልቅልቅታ

ለ. ልጁ ምን እያደረገ ነው?

ሥዕል 4.2 አየር ስለመኖሩ

- ተማሪዎች! በሥዕሎቹ ከተከናወኑት ተግባራት ምን ተረዳችሁ? እናንተም ከመምህራችሁ ጋር በመሆን ተመሳሳይ ሙከራዎችን ተግባራዊ አድርጉ።
- በተጨማሪም በአየር የተሞላን ፊኛ ወደ ላይ ልቀቁ። ፊኛው ምን ሆነ? ለምን እንዲህ ሊሆን እንደቻለ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።

## ለ. የአየር ጥቅም

ተማሪዎች! አየር ለምን ለምን ይጠቅማል?
ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሶቹን ለመምህራችሁ ንገሩ።

ተማሪዎች ከዚህ በታች ያሉትን ሥዕሎች በደንብ ተመልከቱ።



በመተንፈስ ላይ ያለ ልጅ



በአየር የተሞሉ ፊኛዎች



የመኪና ጎማ አየር ሲሞላ

ሥዕል 4.3 የአየር ጠቀሜታ

ሕይወት ያላቸው ነገሮች ለመኖር አየር ያስፈልጋቸዋል። በተጨማሪም አየር የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ይጠቅማል። እንስሳትና ተክሎች ለመተንፈስ አየር ያስፈልጋቸዋል።

## መልመጃ 4.2

ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ።

1. የሰው ልጆች ያለ አየር መኖር ይችላሉ።
2. የመኪና ጎማ ለመሄድ አየር መሞላት አለበት።
3. ዕፅዋት አየር አያስፈልጋቸውም።

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. ሰዎች የሚተነፍሱት ነገር ምንድን ነው?
2. ተክሎች አየር ባያገኙ ምን ይሆናሉ?

## 4.2.2. ውኃ

### ሀ. የውኃ መገኛ

**ተማሪዎች! ውኃ የት የት ይገኛል? ከጓደኞቻችሁ ጋር እየተወያያችሁ በዝርዝር ጻፉ።።**
**በአካባቢያችሁ ውኃ ከየት ከየት እንደሚገኝ ጥቀሱ።።**

**የሚከተሉትን ሥዕሎች ተመልከቱ**



የቧንቧ ውኃ



የጉድጓድ ውኃ



የሐይቅ ውኃ



የምንጭ ውኃ



የወንዝ ውኃ



የዝናብ ውኃ

ሥዕል 4.4 የውኃ መገኛ

**ተማሪዎች! ውኃ ከምን ከምን እንደሚገኝ ከሥዕሎቹ ተገነዘባችሁ?**

**የውኃ መገኛዎች ብዙ ናቸው።**

## ውኃ

- ከሏንሏ
- ከጉድጓድ
- ከኩሬ
- ከሐይቅ
- ከምንጭ
- ከውቅያኖስ
- ከወንዝ
- ከባሕር
- ከዝናብ ይገኛል።

## ሀ. የውኃ ጥቅም

**ውኃ ለምን ለምን ይጠቅማል? ያለ ውሃ መኖር እንችላለን? ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሶቹን ለመምህራችሁ ተናገሩ።**

**ተማሪዎች! ከዚህ በታች ያለውን ሥዕል ተመልከቱ።**



ልጁ ምን እያደረገ ነው?



ሴትየዋ ምን እየሠራች ነው?



በሥዕሉ የሚታየው እንስሳ ምን እያደረገ ነው?




ከሥዕሉ ምን ትረዳላችሁ?



ሥዕሉ ምን ያሳያል?



በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው?



ልጅቷ ምን እያደረገች ነው?

**ሥዕል 4.5 የውኃ ጥቅም**

ውኃ ለሰዎችና ለእንስሳት በመጠጥነት ያገለግላል። ተክሎችም ለዕድገታቸውና ምግባቸውን ለማዘጋጀት ውኃ ይፈልጋሉ። በተጨማሪም ውኃ ለግል ንጽሕና መጠበቂያ፣ ለልብስና ለዕቃ ማጠቢያ እንዲሁም ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን ይጠቅማል።

## መልመጃ 4.3

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. እናንተ የምትጠጡት ውኃ የሚገኘው ከየት ነው?
2. የወንዝ ውኃ ቢጠጣ ምን ችግር ያስከትላል?
3. የውኃ መገኛ ከሆኑት ውስጥ ሦስቱን ጥቀሱ።

## አፈር

ተማሪዎች! አፈር ለምን ለምን ይጠቅማል? ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ መልሶቹን ለመምህራችሁ ንገሩ::

የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ጥያቄዎቹን መልሱ::



ዛፉ ቀጥ ብሎ እንዲቆም ያስቻለው ምንድ ነው?



ሥዕሉ ምንን ያሳያል?

ሥዕል 4.6 የአፈር ጥቅም

ከዚህ በታች የሚታዩት ሥዕሎች ምን ምን ናቸው? ከምን ከምን የተሠሩ ይመስላችኋል?



ይህ ሥዕል ምንን ያሳያል?



ሥዕሉ የሚያሳየው ምንን ነው?



በሥዕሉ የሚታየው ምንድነው?

ሥዕል 4.7 ከአፈር የሚሠሩ መገልገያ ዕቃዎች

**ተማሪዎች!**

**አፈር፡-**

- ለእርሻ ሥራ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው።
- ተክሎች እንዳይወድቁና ቀጥ ብለው እንዲቆሙ ይረዳል።
- ተክሎች በሥሮቻቸው አማካኝነት ውኃ እንዲስቡ ያስችላቸዋል።
- የቡና ጀበና፣ የሸክላ ድስትና የእንጀራ ምጣድ እንዲሁም መሳይ ቅርጾችን ለመሥራት ያገለግላል።

## መልመጃ 4.4

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሱ።**

1. አፈር ለምን ይጠቅማል?
   ሀ. ቤት ለመሥራት
   ለ. ተክሎች ቀጥ ብለው እንዲቆሙ ለመርዳት
   ሐ. ተክሎች በሥሮቻቸው አማካኝነት ውኃ እንዲስቡ ለመርዳት
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው
2. ከሚከተሉት ውስጥ ከአፈር የማይሠራው የቱ ነው?
   ሀ. የቡና ጀበና ሐ. መኪና
   ለ. ማሰሮ መ. የእንጀራ ምጣድ

**ተግባራዊ ሥራ**

ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ሸክላ አፈር በመፈለግ የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## 4.3. በዙሪያችን የሚገኙ ሕይወት ያላቸው ነገሮች

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፡- <br>• ተክሎችን በመጠናቸው ለይታችሁ ትመድባላችሁ። <br>• የተክሎችን ጠቀሜታ ትናገራላችሁ። <br>• ስለተክሎች እንክብካቤ ትናገራላችሁ። <br>• የቤትና የዱር እንስሳትን ትለያላችሁ። <br>• የእንስሳትን ጥቅሞች ትናገራላችሁ <br>• ስለ እንስሳት እንክብካቤ ትገልጻላችሁ። |

**ቁልፍ ቃላት**

- ሕይወት ያላቸው ነገሮች
- ተክሎች
- የቤት እንስሳት
- የዱር እንስሳት

## 4.3.1 ተክሎች

**ተማሪዎች!** በአካባቢያችሁ ምን ምን የተክል ዓይነቶች ይገኛሉ?
በአካባቢያችሁ የሚገኙ ተክሎች ለምን ለምን ይጠቅማሉ?
ከመምህራችሁ ጋር በትምህርት ቤታችሁ አካባቢ የሚገኙትን ተክሎች ተመልከቱ::
በጉብኝታችሁ ወቅት የምትመለከቷቸውን ተክሎች ዛፎች፣ ቁጥቋጦዎችና ትናንሽ ተክሎች በማለት መድቧቸው:: ከዚያም ወደ ክፍላችሁ በመመለስ ውይይት አድርጉ::

**የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ስማቸውንና ለምን እንደሚጠቅሙ ግለጹ::**



በሥዕሉ የሚታየው ተክል ምንድነው?
ለምን ይጠቅማል?



በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው?
ተክሉ ለምን ይጠቅማል?



ይህ ተክል ምን ይባላል? የሚሰጠው
ጥቅም ምንድ ነው?



ይህ ሥዕል የሚያሳየው ምንን ነው?
ተክሉ ለምን ይጠቅማል?



በሥዕሉ የሚታየው ተክል ምንድን ነው? ለምን ይጠቅማል?



ይህ ሥዕል ምንን ያሳያል? ተክሉ ለምን ይጠቅማል?



ይህ ሥዕል የሚያሳየው ምንን ነው? ተክሉ ለምን ይጠቅማል?



በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው? ተክሉ ለምን ይጠቅማል?

**ሥዕል 4.8 የተክል ዓይነቶችና ጠቀሚታቸው**

## ተክሎችን መመደብ

**ተማሪዎች!** የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ በመገልበጥ በመጽሐፋችሁ በሥዕል 4.8 የሚታዩትን የተክል ዓይነቶች ዛፍ፣ ቁጥቋጦና ትንሽ ተክል በማለት መድቡ::

**በተሰጠው ምሳሌ መሠረት የሚከተለውን «✓» ምልክት አስቀምጡ::**

| | የተክሉ ስም | የተክሉ ምድብ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዛፍ | ቁጥቋጦ | ትንሽ ተክል |
| 1 | ዘንባባ | ✓ | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |
| 5 | | | | |
| 6 | ቲማቲም | | | ✓ |
| 7 | | | | |
| 8 | | | | |
| 9 | | | | |

ተክሎች የተለያየ ጠቀሜታ አላቸው። ለምሳሌ፡-

- ለምግብነት
- ለጌጣጌጥ መሥሪያነት
- ለውበትነት
- ለአጥር
- ለቤት ግንባታ
- ለማገዶነትና ለመሳሰሉት ይጠቅማሉ።

## ለተክሎች የሚደረግ እንክብካቤ

**ተማሪዎች! ተክሎችን መንከባከብ ለምን ያስፈልጋል? እናንተ በመኖሪያ ቤታችሁና በትምህርት ቤታችሁ ለሚገኙ ተክሎች ምን ምን እንክብካቤ ታደርጋላችሁ?**

**የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ለተክሎች የሚደረግላቸውን እንክብካቤና ጠቀሜታ ለንደኛችሁ ግለጹ።**



**በሥዕሉ የሚታዩት ልጆች ምን እያደረጉ ነው? የሚያደርጉት እንክብካቤ ለምን ይጠቅማል?**



**ከሥዕሉ ምን ተረዳችሁ? ይህ ተግባር ምን ያስከትላል?**



ልጆቹ ምን እየሠሩ ነው? ይህ ተግባር ለምን ይጠቅማል?

ሥዕል 4.9 ለተክሎች የሚደረግ እንክብካቤ

**ተማሪዎች!** ለተክሎች የሚደረጉ እንክብካቤዎችንና ጠቀሜታቸውን ቀጥሎ ከቀረበው ሠንጠረዥ ተመልከቱ::

## ሠንጠረዥ 4.1 የተክሎች እንክብካቤና ጠቀሜታቸው

| ተ.ቁ | የእንክብካቤ ዓይነት | እንክብካቤ የሚሰጠው ጠቀሜታ |
|---|---|---|
| 1 | ውኃ ማጠጣት | ተክሎች እንዳይጠወልጉ ይረዳል:: |
| 2 | አረም ማረም | ተክሎች እንዳይቀጭጩ ይጠቅማል:: |
| 3 | መኮትኮት | በቂ አየር እንዲያገኙ ያግዛል:: |
| 4 | ማደበሪያ መስጠት | ተክሎች እንዲፋፉ ይጠቅማል:: |
| 5 | በእንስሳት እንዳይጎዱ መጠበቅ | ተክሎች እንዳይደርቁ ይረዳል:: |
| 6 | ያለ አግባብ አለመቁረጥ | ተክሎች እንዳይደርቁ ይጠቅማል:: |
| 7 | ንጽሕናቸውን መጠበቅ | ተክሎች እንዳይደርቁና በበሽታ እንዳይጐዱ ይረዳል:: |

## መልመጃ 4.5

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::**

1. ተክሎች ከሚሰጡት ጥቅም ሦስቱን ግለጹ::
2. በተክሎች ላይ ቆሻሻ ውኃ መድፋት ምን ችግር ያስከትላል?
3. ተክሎችን ለመንከባከብ ምን ምን ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል?
4. ቲማቲምና ካሮት ከየትኛው የተክል ዓይነት ይመደባሉ?
5. አረምን ማረም ለምን ይጠቅማል?

## 4.3.2 እንስሳት

### ሀ. የእንስሳት አመዳደብ

**ተማሪዎች! ምን ምን ዓይነት እንስሳትን ታውቃላችሁ?**

**የቤት እንስሳት ምንድን ናቸው?**

**የዱር እንስሳት ምንድን ናቸው?**

**የቤት እንስሳት፡-** ከሰዎች ጋር ተጠግተው የሚኖሩ ለማዳ እንስሳት ናቸው።

**የዱር እንሰሳት፡-** ከሰዎች ርቀው በዱር (በጫካ) ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት ናቸው።


**የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት እንስሳቱን የቤትና የዱር እንስሳት በማለት መድቧቸው።**



**በሥዕሉ የሚታየው እንስሳ ምንድን ነው? እንስሳው በየትኛው ምድብ ይገኛል?**




**ሥዕሉ ምንን ያሳያል? የሚገኝበትን ምድብ ግለጹ።**



**ይህ የምን ሥዕል ነው? በየትኛው ምድብ ይገኛል?**




**በሥዕሉ የሚታየው ምንድንነው? ምድቡን ግለጹ።**



ሥዕሉ ምንን ያሳያል? በምን ምድብ ውስጥ ይገኛል?



በሥዕሉ የሚታየው እንስሳ ምንድነው? የሚገኝበትን ምድብ ግለጹ



ይህ የምን ሥዕል ነው? ምድቡን ተናገሩ።



ሥዕሉ ምንን ያሳያል? በየትኛው ምድብ ይገኛል?



በሥዕሉ የሚታየው እንስሳ ምን ይባላል? በየትኛው ምድብ ይገኛል?

**ሥዕል 4.10 የቤትና የዱር እንስሳት**

**ተማሪዎች!** በሥዕሉ ላይ የቀረቡት እንስሳት በግ፣ አህያ፣ ድመት፣ ዶሮና ላም የቤት እንስሳት (ለማዳ እንስሳት) ሲሆኑ ነብር፣ ዝንጀሮና አንበሳ ደግሞ የዱር እንስሳት ናቸው።

## ለ. የእንስሳት ጥቅም

በሚከተለው ሠንጠረዥ የቀረበውን ምሳሌ በማድረግ እያንዳንዱ እንስሳ የሚሰጠውን ጥቅም ጻፉ::

| የእንስሳው ስም | እንስሳው የሚሰጠው ጥቅም |
|---|---|
| ላም | ወተት፣ ሥጋ |
| ዶሮ | |
| በግ | |

## ተግባራዊ ክንውን

በሚከተለው ሠንጠረዥ የቀረበውን ምሳሌ በማድረግ እያንዳንዱን ጥቅም የሚሰጡ እንስሳትን ስም ጻፉ

| የእንስሳው ስም | ከእንስሳው የሚገኘው ጥቅም |
|---|---|
| አህያ | ዕቃን ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ ይጠቅማል:: |
| | ለእርሻ ሥራ ያገለግላል:: |
| | ጋሪ ይጎትታል:: |
| | ፀጉሩ ለልብስ መሥሪያነት ይጠቅማል:: |
| | ቤትን ከሌባ ይጠብቃል:: |
| | አይጥ የሚያደርሰውን ጥፋት ይከላከላል:: |

የእንስሳት ዋና ዋና ጥቅሞች የሚከተሉት ናቸው::

- ለምግብነት
- ለመጓጓዣነት
- ለመዝናኛነት
- ለገቢ ምንጭነት
- ለጥበቃ ሥራ
- ለአልባሳትና ለመሳሰሉት በጥሬ ዕቃነት ያገለግላሉ::

## መልመጃ 4.6

**ሀ. በ«ሀ» ሥር የቀረቡትን በ«ለ» ሥር ከቀረቡት ጋር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ቀንድ | ሀ. የብርድ ልብስ ለመሥራት ይጠቅማል |
| 2. ጠፍር | ለ. ለምግብነት ይጠቅማል |
| 3. ቆዳ | ሐ. ለጌጣጌጥ መሥሪያ ይጠቅማል |
| 4. የበግ ፀጉር | መ. ለአልጋ መሥሪያ ያገለግላል |
| 5. የዱር እንስሳ | ሠ. ለገቢ ምንጭነት ይጠቅማል |
| | ረ. ለጫማ መሥሪያ ይጠቅማል |
| | ሰ. ለመድኃኒትነት ያገለግላል |

**ሐ. ለእንስሳት እንክብካቤ ማድረግ**

**ተማሪዎች!** እንስሳትን ለምን እንከባከባለን?

ለእንስሳት የሚደረግ እንክብካቤ መገለጫዎች ምን ምንድን ናቸው?

ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለመምህራችሁ ግለጹ።

**የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ለእንስሳቱ የሚደረገውን እንክብካቤ ግለጹ።**



በሥዕሉ የምትታየው ድመት ምን እያደረገች ነው?



ልጅቷ ምን እያደረገች ነው?





እንስሳቱ ምን እያደረጉ ነው?

ሥዕል 4.11 ለእንስሳት የሚደረግ እንክብካቤ

**ተማሪዎች!** እንስሳት ጤናማ እንዲሆኑና ተገቢውን ጥቅም እንዲሰጡን እንክብካቤ ልናደርግላቸው ይገባል። እንስሳትን፦

- በመመገብ
- ውሃ በማጠጣት
- መጠለያቸውን በመጠበቅ
- ንጽሕናቸውን በመጠበቅ
- ባለመምታት
- ባለመተናኮል መንከባከብ ይኖርብናል።

## መልመጃ 4.7

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. የእንስሳትን ንጽሕና በመጠበቅ የምንከባከበው ለምንድን ነው?
2. እንሰሳትን መተናኮል ምን ያስከትላል?
3. ለእንስሳት ምግብ በመስጠት የምንከባከበው ለምንድን ነው?

## 4.4 በአካባቢያችን የተስመዱ የሥራ ዓይነቶች

| ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች |
| --- |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦<br>• የሥራን ጠቀሜታ ትናገራላችሁ።<br>• የሥራ ዓይነቶችን የግል ሥራ፣ በግለሰብ በመቀጠር የሚሠራ ሥራና የመንግሥት ሥራ በማለት ትመድባላችሁ።<br>• በአካባቢያችሁና በቤቶቻችሁ የሚከናወኑ ቀላል ሥራዎችን በተግባር ታሳያላችሁ። |

**ቁልፍ ቃላት**

- ሥራ
- የሥራ ዓይነቶች

## 4.4.1. የሥራ ጥቅም

**ተማሪዎች!** ሥራ መሥራት ለምን ይጠቅማል?

በወረዳችሁ ነዋሪዎች በስፋት የተለመዱ የሥራ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?

ሥራ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ይጠቅማል። የማይሠሩ ሰዎች ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማግኘትና ሕይወታቸውን መለወጥ አይችሉም። ስለዚህ ሥራ ራስን ለመቻልና የሌሎች ጥገኛ ላለመሆን የሚከናወን ተግባር ነው።

**ተማሪዎች!** ወላጆቻችሁ ሥራ በመሥራት ገቢ ባያገኙ ኖሮ ምን ዓይነት ችግር ይኖር ነበር?

## 4.4.2. የሥራ ዓይነቶች

**ተማሪዎች!** የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።




- ሥዕሉ ምንን ያሳያል?
- በሥዕሉ የሚታየው ሰው የሚተዳደረው በምንድን ነው?



- በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው?
- በሥዕሉ የሚታየው ሰው እያከናወነ ያለው ስራ ምን በመባል ይታወቃል?





- በሥዕሉ የምትታየው ሴት የምትሠራው ሥራ ምንድን ነው?

በሥዕሉ የምትታየው ሴት የተሠማራችው በምን ሙያ ነው?





- ሥዕሉ የሚያሳየው ምንን ነው?
- በሥዕሉ የሚታየውና ነጭ ገዋን የለበሰው ሰው በምን ይተዳደራል?

- በሥዕሉ የሚታዩት ሰዎች የሚተዳደሩት በምንድን ነው?

**ሥዕል 4.12 የሥራ ዓይነቶች**

የሥራ ዓይነቶች በሦስት ይመደባሉ:: እነርሱም:-

- የመንግሥት ሥራ
- የግል ሥራና
- ለግለሰብ ተቀጥሮ መሥራት ናቸው::

## መልመጃ 4.8

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ የመልሱን ፊደል አክብቡ።**

1. ከሚከተሉት ውስጥ የመንግሥት ሥራ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የጉልት ንግድ ሐ. ሽመና
   ለ. የሸክላ ሥራ መ. ዳኝነት
2. ከሚከተሉት የግል ሥራ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ፖሊስነት ሐ. ልብስ ስፌት
   ለ. ዳኝነት መ. የወረዳ አስተዳዳሪነት
3. ከሚከተሉት ውስጥ የሥራ ጥቅም ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. መሠረታዊ ፍላጐት ማሟላት ሐ. የሌሎች ጥገኛ መሆን
   ለ. ሕይወት መለወጥ መ. ራስን መቻል
4. ከሥራ ዓይነት የማይመደበው የትኛው ተግባር ነው?
   ሀ. የጉልት ንግድ ሐ. የጉልበት ሥራ
   ለ. ልመና መ. የጽዳት ሥራ

### 4.4.3 በሥራ መኩራት

**ተማሪዎች!** ቤተሰቦቻችሁን ምን ምን ሥራዎችን በመሥራት ታግዛላችሁ?
ቤተሰብን በሥራ ማገዝ የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ንገሩ።

**የሚከተሉትን ሥዕሎች በመመልከት ለጥያቄዎቹ መልስ ስጡ።**



በሥዕሉ የሚታየው ልጅ ምን እያደረገ ነው?



በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው?



ሥዕሉ ምንን ያሳያል?



ልጅቷ ምን እያደረገች ነው?

ሥዕል 4.13 ቤተሰብን በሥራ መርዳት

**ተማሪዎች!** ቤተሰብን የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን መርዳት ይኖርብናል። በቤታችን ውስጥ በአቅማችን የምናከናውነው ሥራ አካላችን እንዲጠነክር፣ ሥራን እንድንለምድና ቤተሰቦቻችንን እንድናግዝ ይረዳናል። ስለዚህም በቤታችን ውስጥ በምንሠራው ሥራ ኩራት ሊሰማን ይገባል።

## መልመጃ 4.9

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. በግብርና ሙያ የተሰማሩ ሰዎች ሥራቸውን በደንብ ባይሠሩ ምን ሊከሰት ይችላል?
2. የመኪና አሽከርካሪ መኪናውን በአግባቡ ባያሽከረክር ምን ሊፈጠር ይችላል?
3. በዳቦ ቤት ዳቦ የሚጋግሩ ሰዎች ዳቦውን በንጽሕና ባይጋግሩ ምን ዓይነት ችግር ሊፈጠር ይችላል?
4. ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ባይማሩ ምን ችግር ይፈጠራል?

## 4.5 የአካባቢያችን መጓጓዣ

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች**

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦**

- የመጓጓዣን ጠቀሜታ ትናገራላችሁ።
- የባህላዊ የመጓጓዣ ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ።
- የዘመናዊ መጓጓዣ ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ።

**ቁልፍ ቃላት**

- ባህላዊ መጓጓዣ
- ዘመናዊ መጓጓዣ

## 4.5.1 የመንገዝ ጥቅም

**ተማሪዎች! መንገዝ ምንድን ነው? ምንስ ጥቅም ይሰጣል? ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ።**

**መንገዝ ሰውን ወይም ዕቃን ከቦታ ቦታ የምናንቀሳቅስበት ነገር ነው።**
**የመንገዝ ዓይነቶች ሁለት ናቸው። እነርሱም፦**

1. **ባህላዊ መንገዝና**
2. **ዘመናዊ መንገዝ ናቸው።**

### 1. ባህላዊ መንገዝ

**ተማሪዎች! የሚከተሉትን ሥዕሎች በጥንቃቄ በመመልከት ለጥያቄዎቹ መልስ ስጡ።**



**በሥዕሉ የሚታየው ምንድን ነው?**
**ይህ እንስሳ ለምን ይጠቅማል?**



**ሥዕሉ ምንን ያሳያል? ይህ እንቅስቃሴ**
**በስፋት የሚታየው በየት አካባቢ ነው?**



**በሥዕሉ የሚታው እንስሳ በየት አካባቢ**
**ይገኛል? ለምንስ ይጠቅማል?**



**ሥዕሉ ምንን ያሳያል? ለምንስ ያገለግላል?**

**ሥዕል 4.14 ባህላዊ የመንገዝ ዓይነቶች**

## 2. ዘመናዊ መጓጓዣ

**ተማሪዎች!** ዘመናዊ መጓጓዣ ማለት ምን ማለት ነው? ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሱን ለመምህራችሁ ንገሩ::

**ተማሪዎች! ሥዕሱን በመመልከት የጥያቄዎችን መልሶች ለመምህራችሁ ንገሩ::**



በሥዕሉ የሚታየው የመጓጓዣ ዓይነት ምን ይባላል? ለምንስ ይጠቅማል?



ሥዕሉ የሚያሳየው ምንን ነው? ይህ የመጓጓዣ ዓይነት ምን ጥቅም ይሰጣል?




ሥዕሉ ምንን ያሳያል? ይህ የመጓጓዣ ዓይነት ከሌሎቹ የሚለየው በምንድን ነው?



ይህ የመጓጓዣ ዓይነት ምን ይባላል? ከሌሎቹ በምን ይለያል?

**ሥዕል 4.15 ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች**

**ተማሪዎች!** አህያ፣ ፈረስ፣ በቅሎ፣ ግመልና ጋሪ ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ናቸው:: ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች የመኪና መንገድ በሌለባቸው አካባቢዎች ሰዎችንና ዕቃን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ይጠቅማሉ:: ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነት መኪናን፣ ባቡርን፣ አውሮፕላንን፣ መርከብንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል:: ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ፈጣን ናቸው::

## መልመጃ 4.10

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. የመጓጓዣ ዓይነቶች በስንት ይመደባሉ? ስማቸውን ጥቀሱ፡፡
2. አህያ በየትኛው የመጓጓዣ ዓይነት ውስጥ ይመደባል?
3. መጓጓዣ ለምን ለምን ይጠቅማል?
4. ፈጣን ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነት ማለት ምን ማለት ነው?
5. የመኪና መንገድ በሌለበት አካባቢ ሰዎችን ለማጓጓዝ የሚያገለግለው የመጓጓዣ ዓይነት ምን ይባላል?
6. ብዙ ሰዎችንና ዕቃዎች በአንድ ጊዜ ለማጓጓዝ የሚያስችለው የመጓጓዣ ዓይነት ምን ይባላል?

# ማጠቃለያ

- አቅጣጫ አንድን ቦታ ለመጠቆም ወይም ለማመልከት የምንጠቀምበት መንገድ ነው። ግራ፣ ቀኝ፣ ከፊት፣ ከኋላ፣ አጠገብ፣ መካከል የሚሉትን ስያሜዎች በመጠቀም የአንድን ነገር መገኛ ማመልከት ይቻላል።
- በአካባቢያችን የተለያዩ ሕይወት የሌላቸው ጠቃሚ ነገሮች ይገኛሉ። አየር፣ አፈርና ውኃ በአካባቢያችን የሚገኙ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ናቸው። አፈር ለተክሎች ዕድገት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ውኃ ለእንስሳትና ለዕፅዋት ሕልውና እጅግ አስፈላጊ ነው። ውኃ ለመጠጥነት፣ ለማጠቢያ፣ ለተክሎች፣ ለምግብ ማብሰያነት ይጠቅማል። ውኃ ከዝናብ፣ ከወንዝ፣ ከጉድጓድ፣ ከምንጭ፣ ከሏንሏና ከመሳሰሉት ሊገኝ ይችላል።
- እንስሳትና ዕፅዋት በአካባቢያችን የሚገኙ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ናቸው። ዕፅዋት (ተክሎች) በመጠናቸው ዛፎች፣ ቁጥቋጦዎችና ትናንሽ ተክሎች ተብለው ይመደባሉ። እንስሳት ደግሞ የዱር እንስሳት እና የቤት እንስሳት ተብለው ይመደባሉ። የዱር እንስሳት ከሰው ርቀው በየዱሩና በየበረሃው ይኖራሉ። የቤት እንስሳት ደግሞ ከሰው ተጠግተውና ተላምደው ይኖራሉ። እንስሳትና ዕፅዋት ለሰው ልጆች በጣም ጠቃሚ ናቸው።
- በአካባቢያችን በስፋት የተለመዱ ልዩ ልዩ የሥራ ዓይነቶች አሉ። የሥራ ዓይነቶች የመንግሥት ሥራ፣ የግል ሥራ እና ለግለሰብ ተቀጥሮ መሥራት ተብለው ይመደባሉ። ሥራ ምግብን፣ ልብስንና መጠለያን ለማግኘት ይጠቅማል።
- መጓጓዣ ሰዎችንና ዕቃን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ይጠቅማል። የመጓጓዣ ዓይነቶች ባህላዊና ዘመናዊ ተብለው ይከፈላሉ። ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች የመኪና መንገድ በሌለባቸው አካባቢዎች ሰዎችንና ዕቃን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ይጠቅማሉ። ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ደግሞ ብዙ ሰዎችንና በርካታ ዕቃዎችን በአንድ ጊዜ ለማጓጓዝ ይረዳሉ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ::**

1. ልጆች ምንም ዓይነት ሥራ መሥራት የለባቸውም::
2. አየር፣ አፈር እና ውኃ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ናቸው::
3. ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ፈጣንና ርካሽ ናቸው::
4. ውሻ የዱር እንስሳ ነው::
5. ሥራ መሥራት ምንም ጥቅም የለውም::

**ለ. በ"ሀ" ሥር የተቀመጡትን በ"ለ" ሥር ካሉት ጋር አዛምዱ::**

| #ሀ; | #ለ; |
|---|---|
| 1. ግራና ቀኝ | ሀ. ለመተንፈስ ይጠቅማል |
| 2. አየር | ለ. የዱር እንስሳ |
| 3. ዶሮ | ሐ. የዱር እንስሳት መኖሪያ |
| 4. ነብር | መ. የቤት እንስሳት መኖሪያ |
| 5. ደን | ሠ. አቅጣጫዎች |
| | ረ. የቤት እንስሳ |
| | ሰ. ባህላዊ መጓጓዣ |
| | ሸ. ዘመናዊ መጓጓዣ |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::**

1. ከሚከተሉት ውስጥ ሕይወት ያለው ነገር የትኛው ነው?

   ሀ. ውኃ ለ. ተክል ሐ. አፈር መ. አየር

2. የውኃ ጥቅም የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ለመጠጥ ሐ. ለንፅህና

   ለ. ለተክሎች እድገት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

3. ተክሎች ለምን ጥቅም ይውላሉ?

   ሀ. ለምግብነት ሐ. ለአካባቢ ውበት

   ለ. ለማገዶ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

4. ከሚከተሉት ውስጥ የዱር እንስሳ የሆነውን ለዩ::

   ሀ. ነብር ለ. ድመት ሐ. በግ መ. አህያ

5. እንስሳትን እንዴት መንከባከብ እንችላለን?

   ሀ. በመመገብ ሐ. ባለመተናኮል

   ለ. መጠለያ በማዘጋጀት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

## ፍተሻ

*ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሳጥኖች ውስጥ በማስቀመጥ አመልክቱ::*

1. የትምህርት ቤቴን፣ የመኖሪያ ቤቴንና የወረዳዬን አንጻራዊ መገኛ ማመልከት እችላለሁ:: ☐
2. የአየር፣ የውሃና የአፈር ባሕርያትን እገልጻለሁ፣ ጥቅማቸውን አስረዳለሁ:: ☐
3. አፈር (ጭቃ) በመጠቀም የተለያዩ መሳይ ቅርጾችንና ምስሎችን እሠራለሁ:: ☐
4. ተክሎችን በመጠናቸውና በዓይነታቸው በመመደብ ጥቅማቸውን እናገራለሁ፤ ሊደረግላቸው የሚገባውን እንክብካቤም በተግባር አሳያለሁ:: ☐
5. እንስሳትን የቤትና የዱር እንስሳት በማለት በመመደብ ጥቅማቸውን እናገራለሁ:: ለእንስሳት የሚደረገውን እንክብካቤ እገልጻለሁ:: ☐
6. የተለያዩ የሥራ ዓይነቶችን የግል ሥራና የመንግሥት ሥራ ብዬ በመመደብ የሥራ ጥቅምን እናገራለሁ:: ☐
7. ለሥራ ያለኝን ክብርና ፍቅር በተግባር አሳያለሁ:: ☐
8. የመጓጓዣን ጥቅም በመናገር የባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣ ምሳሌዎች እሰጣለሁ:: ☐
9. ሳይንሳዊ የምርምር ክህሎቶችን ማለትም መመልከትን፣ መጠየቅን፣ መግባባትን፣ ተባብሮ መሥራትንና መመደብን በተግባር አሳያለሁ:: ☐